# ያላግባብ ፡ በመበልጸግ ፡ ላይ ፡ የሚመሠረት ፡ ክስ ፡ ሊቀርብ ፡ የሚችለው ፡ በመጨረሻ ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ሲገኝ ፡ (ሰብሲዲያሪቲ ፡ ሲኖረው) ፡ ነው ፡ የሚለው ፡ መሠረተ አሳብ ፡ በፈረንሳይና ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ።

ከሠመረአብ ፡ ሚካኤል ።

## መግቢያ ፡

የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ዓላማ ፡ ያላግባብ ፡ በመበልጸግ ፡ ላይ ፡ የሚመሠረት ፡ ክስ ፡ ሊቀርብ ፡ የሚችለው ፡ በመጨረሻ ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ሲገኝ ፡ (ሳብሲዲያሪቲ ፡ ሲኖረው) ነው ፡ የሚለው ፡ መሠረተ ፡ አሳብ ፡ በፈረንሣይ ፡ ሕግና ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ የሚሰጠውን ፡ ትርጉም ፡ መመርመር ፡ ነው ። የሚከተለው ፡ ስለ ፡ ጽሑፉ ፡ አቀራረብ ፡ አጭር ፡ መግለጫ ፡ ነው ።

የነገሩን ፡ አመጣጥ ፡ ለመረዳት ፡ ይረዳን ፡ ዘንድ ፡ የሮማውያን ፡ ሕግና ፡ የፈረንሣይ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ስላላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ምን ፡ እንደሚሉ ፡ ባጭሩ ፡ እንመለከታለን ። ቀጥለንም ፡ የፈረንሣይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶችና ፡ ጸሐፊዎች ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ የሚለውን ፡ አሳብ ፡ እንዴት ፡ አንድ ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ የግዴታዎች ፡ ምንጭ ፡ ለመሆን ፡ እንዳበቁት ፡ እንመለከታለን ።

ሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ያላግባብ ፡ በመበልጸግ ፡ ላይ ፡ የሚመሠረት ፡ ክስ ፡ ሊቀርብ ፡ የሚችለው ፡ "በመጨረሻ ፡ ደረጃ" ላይ ፡ መሆኑን ፡ የሚገልጸው ፡ መሠረተ ፡ አሳብ ፡ በፈረንሳይ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ምን ፡ ትርጓሜ ፡ እንዳለው ፡ የሚያሳይ ፡ ይሆናል ። ወደዚህ ፡ መሠረተ ፡ አሳብ ፡ ከመግባታችን ፡ በፊት ፡ "በቂ ፡ ምክንያት" ፡ የሚለውን ፡ መሠረተ ፡ አሳብ ፡ ባጭሩ ፡ እንመረምራለን ። ይህም ፡ የሆነበት ፡ ምክንያት ፡ በሁለቱ ፡ መሠረተ ፡ አሳቦች ፡ መካከል ፡ ግንኙነት ፡ ስላለና ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕግ ፡ ለመረዳት ፡ ሁለቱን ፡ አሳቦች ፡ ጠንቅቆ ፡ ማወቅ ፡ ስለሚያስፈልግ ፡ ነው ።

ይህ ፡ "የመጨረሻ ፡ ደረጃነት ፡" ("ሳብሲዲያሪቲ") ፡ የሚለው ፡ አነጋገር ፡ አያሌ ፡ መሠረተ ፡ አሳቦችን ፡ ያዘለ ፡ በመሆኑ ፡ አራት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሁኔታዎችን ፡ ወይም ፡ የፍርድ ፡ ጉዳዮችን ፡ በመተንተን ፡ የሚብራራ ፡ ይሆናል ። ከያንዳንዱ ፡ የፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ ግርጌ ፡ የፈረንሣይ ፡ የሕግ ፡ አዋቂዎች ፡ ያቀረቧቸው ፡ መፍትሔዎችና ፡ የፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ውሳኔዎች ፡ ቀርበዋል ። ከዚያም ፡ "የመጨረሻነት ፡ ደረጃ ፡" ("ሳብሲዲያሪቲ") ፡ የሚለውን ፡ መሠረተ ፡ አሳብ ፡ ለምን ፡ እንደተፈጠረ ፡ የሚገልጹትን ፡ ባሕረ ፡ አሳቦችንና ፡ ይህ ፡ መሠረተ ፡ አሳብ ፡ "በቂ፡ ምክንያት"፡ ከሚለው ፡ አሳብ፡ ጋር፡ እንዴት፡እንደሚደራረብ፡እንመለከታለን። የዚህ፡ዓይነቱ፡አቀራረብ፡ጠቃሚነቱ፡ በሁለት፡ ረገድ ፡ ነው ። በመጀመሪያ ፡ በፈረንሣይ ፡ ሕግ ፡ ያለውን ፡ ሁኔታ ፡ የሚገልጽ ፡ ይሆናል ፤ በይበልጥ ፡ ደግሞ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ስለዚህ ፡ መሠረተ ፡ አሳብ ፡ በግልጽ ፡ የተነገረ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ ስለማይገኝ ፡ በሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕግ ፡ ለማብራራት ፡ ለምናደርገው ፡ ሙከራ ፡ አንድ ፡ የሃሳብ ፡ ምንጭ ፡ በመሆን ፡ ያገለግላል ።

# ክፍል ፡ ፩ ፡

## "ያላግባብ ፡ መበልጸግ" ፡ ተብሎ ፡ ስለሚታወቀው ፡ ባሕረ ፡ አሳብ ፡ እና ፡ በርሱም ፡ ተመርኩዘው ፡ ስለሚነሱ ፡ ክሶች ፡ ታሪካዊ ፡ መግለጫ ።

### ፩/ የሮማውያን ፡ ሕግ ፡

"ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡" ተብሎ ፡ የሚጠራው ፡ አሳብ ፡ የተፈጠረው ፡ በሮማ ውያን ፡ ሕግ ፡[1] ቢሆንም ፤ ማንኛውንም ፡ አላግባብ ፡ የሚገኝ ፡ ብልጽግና ፡ የሚያወ ግዝ ፡ "የዚህ ፡ ዓይነት ፡ አጠቃላይ ፡ ደንብ ፡ ነበር ፡ ለማለት ፡ አይቻልም ።"[2] ሮማ ውያን ፡ ያደረጉት ፡ በሌላው ፡ አላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ የተበደለ ፡ ሰው ፡ የገንዘብ ፡ ካሣ፡ ለመቀበል ፡ የሚያስችሉትን ፡ በቍጥር ፡ የታወቁ ፡ ክሶችን ፡ (ኮንዲክሲዮኔስ) ፡ ማቋቋ ም ፡ ነበር ።

በተጨማሪ ፡ ቻሊስ ፡ የተባለ ፡ ጸሐፊ ፡ "በሮማውያን ፡ ሕግ ፡ ያላግባብ ፡ የተበለ ጸገበትን ፡ ንብረት ፡ ለማስመለስ ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ ይቻል ፡ ነበር"[3] ፡ ሲል ፡ ጽፏል ። ከነዚህም ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡ አክስዮ ፡ ደ ፡ ኢን ፡ ሬም ፡ ቬርሶ ፡— ተብሎ ፡ የሚጠራው ፡ ነበር። በዚህም ፡ ክስ ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ ባርያ ፡ አለ ፡ ጌታው ፡ ፈቃድ ፡ ውል ፡ ተዋውሎ ፡ በውሉ ፡ መሠረት ፡ ያገኘውን ፡ ብልጽግና ፡ ለጌታው ፡ ቢያስተላልፍ ፡ ሃብቱ ፡ ያላግባብ ፡ የተቀነሰበት ፡ ወገን ፡ ከጌትየው ፡ ሃብቱን ፡ ለማስመለስ ፡ ይችል ፡ ነበር ።

ይህ ፡ ደ ፡ ኢን ፡ ሬም ፡ ቬርሶ ፡ የሚባለው ፡ ክስ ፡ በጊዜ ፡ ብዛት ፡ ሌሎችንም ፡ ያላ ግባብ ፡ ሁኔታዎችን ፡ አጠቃለለ ።

ይህን ፡ ዕድገት ፡ ኒኮላስ ፡ እንደሚከተለው ፡ ገልጾታል ።

"ይህ ፡ አክስዮ ፡ ደ ፡ ኢን ፡ ሬም ፡ ቬርሶ ፡ ተብሎ ፡ የታወቀው ፡ የክስ ፡ አቀራረብ ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ ትርጉም ፡ የተሰጠው ፡ በሮማውያን ፡ ሕግ ፡ በኮዴክስና ፡ ዳይጀስት ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ አንዳንድ ፡ ሃሳቦች ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ነው ። እነርሱም ፡ ተከ ሳሹ ፡ የበለጸገው ፡ በከሳሹና ፡ በአንድ ፡ ነፃ ፡ በሆነ ፡ ሦስተኛ ፡ ሰው ፡ ሳቢያ ፡ በተደ ረገ ፡ ውል ፡ ቢሆንም ፤ አክስዮ ፡ ደ ፡ ኢን ፡ ሬም ፡ ቬርሶ ፡ እንዲያመጣ ፡ ይፈቅዱለት ፡ ነበር ። ቀስ ፡ ብለው ፡ ተችዎችም ፡ በመጀመሪያ ፡ ከሶስተኛ ፡ ወገን ፡ ጋር ፡ በተፈ ጸመ ፡ ውል ፡ ለተፈጠረ ፡ መበልጸግ ፡ ክስ ፡ እንዲቀርብ ፡ ሲፈቅዱ ፡ በመጨረሻ ፡ ደግሞ ፡ ለማንኛቸውም ፡ መበልጸግ ፡ እንዲከፈት ፡ ፈቀዱ"።[4]

---

1. ማዞ ፡ ኤ ፡ ማዞ ፡ ሌሶን ፡ ዴ ፡ ድርዋ ፡ ሲቪል ፡ ፪ኛ ፡ መጽሐፍ ፡ ቀ- ፲፱፻፲፫ ፡ ገጽ ፡ ፯፻፴፯ ።
2. ደብልዩ ፡ በክላንድ ፡ ኤ ፡ ቴክስት-ቡክ ፡ ኦቭ ፡ ሮማን ፡ ሎው ፡ (፫ኛ ፡ እትም ፡ በ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ የተሻሻለ) ፡ ገጽ ፡ ፭፻፳፩ ።
3. ጂ ፡ ቻሊስ ፡ ዘ ፡ ዶክትሪን ፡ ኦቭ ፡ አንጀስቲፋይድ ፡ ኤንሪችሜንት ፡ ኢን ፡ ዘ ፡ ሎው ፡ ኦቭ ፡ ዘ ፡ ፕሮቪ ንስ ፡ ኦቭ ፡ ኩቤክ ፡ (፪ኛ ፡ እትም ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡) ፡ ገጽ ፡ ፪ ።
4. ቢ ፡ ኒኮላስ ፡ "አንጀስቲፋይድ ፡ ኤንሪችሜንት ፡ ኢን ፡ ዘ ፡ ሲቪል ፡ ሎው ፡ ኤንድ ፡ ሉዊዚያና ፡ ሎው፡ ቱሌን ፡ ሎው ፡ ሪቪው ፡ ቮልዩም ፡ ፴፮ ፡ (፲፱፻፷፩-፷፪ ፡ እ- ኤ- አ-) ፡ ገጽ ፡ ፮፻፲፬ ።

## ፪/ የፈረንሣይ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በተደነገገበትና ፡ ቀጥሎ ፡ ባሉት ፡ ጊዜያት ፡ ያለው ፡ ሁኔታ ።

በሌላ ፡ ሰው ፡ በመገልገል ፡ በቂ ፡ ባልሆነ ፡ ምክንያት ፡ ጥቅም ፡ ማግኘት ፡ የተከለከለ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ አጠቃላይ ፡ ሕግ ፡ በፈረንሣይ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ አይገኝም ።[5]

ቢሆንም ፡ ከዚህ ፡ አጠቃላይ ፡ ሕግ ፡ የመነጩ ፡ ዝርዝር ፡ ሕጎች ፡ ይገኛሉ ።[6] ኮሊንና ፡ ካፒታ ፡ ሁኔታውን ፡ እንደሚከተለው ፡ ይገልጻሉ ።

አንድ ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ ያገኘበት ፡ ሁኔታ ፡ ከመጀመሪያ ፡ የማይጸና ፡ ወይም ፡ ወደፊት ፡ የማይጸና ፡ የሚደረግ ፡ ከሆነና ፡ በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ ንብረቱን ፡ እንዲመልስ ፡ ሲገደድ ፤ በንብረቱ ፡ ላይ ፡ አስፈላጊና ፡ ጠቃሚ ፡ ወጪ ፡ በማድረግ ፡ የንብረቱን ፡ ዋጋ ፡ ከፍ ፡ አድርጎት ፡ እንደሆን ፡ ንብረቱ ፡ የጨመረውን ፡ ዋጋ ፡ ልክ ፡ ሊያስቀር ፡ ይችላል ። ቍ ፡ ፰፻፷፩ ፡ እና ፡ ፰፻፷፪ ፡ ስለ ፡ ውርስ ፡ ንብረት ፡ መመለስ ፡ ጉዳይ ፡ሲያብራሩ ፡ እላይ፡ የተባለውን ፡ እንደጠበቁ ፡ ነው ። በቍ ፡ ፩ሺ፮፻፸፫ ፡ መሠረት ፡ የመጀመሪያው ፡ ሽያጭ ፡ መልሶ ፡ የመግዛት ፡ መብቱን ፡ ሊጠቀምበት ፡ ቢፈልግ ፡ ለጥንት ፡ ገዢው ፡ ስላደረገው ፡ ወጪ ፡ ተገቢውን ፡ ካሣ ፡ መክፈል ፡ አለበት ። በሚከተሉትም ፡ ቍጥሮች ፡ ይህ ፡ የተጠበቀ ፡ ሆኗል ። ይኸውም ፡ በቍ ፡ ፩ሺ፫፻፹፩ ፡ መሠረት ፡ ዕቃ ፡ የተመለሰለት ፡ ሰው ፡ ለባለ ፡ ይዞታው ፡ (በቅን ፡ ልቦና ፡ ዕቃውን ፡ ባይዝም ፡) ካሣ ፡ መክፈል ፡ አለበት ፤ በቍ ፡ ፩ሺ፱፻፵፯ ፡ ዕቃ ፡ በአደራ ፡ የተሰጠው ፡ ሰው ፡ ለዕቃው ፡ ጥበቃ፡ ስለሚያወጣው ፡ ወጪ ፡ መክፈል ፡ እንዳለበት ፡ በቍ ፡ ፪ሺ፹ ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ አበዳሪ ፡ መያዣውን ፡ ለመጠበቅ ፡ ስላወጣው ፡ ወጪና ፡ በቍ ፡ ፳፻፸፭ ፡ መሠረት ፡ አንደ ፡ ሶስተኛ ፡ ወገን ፡ መያዣ ፡ የሆነውን ፡ ንብረት ፡ ሲያጣ ፡ ወይም ፡ መንግሥት ፡ ሲወስድበት ፡ ስለሚከፈል ፡ ካሣ ፡ የሚናገር ፡ ነው ።[7] ቍ ፡ ፭፻፵፰ ፡ ፭፻፶፬ ፡ ፭፻፶፭ ፡ ፭፻፷፮ ፡ ፭፻፸ ፡ እና ፡ ፭፻፸፩ ፡ በዋና ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ስለሚጨመሩ ፡ ነገሮች ፡ የሚያትቱ ፡ ሲሆኑ ፡ እላይ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ንጥረ ፡ ሃሳብ ፡ ይከተላሉ ። በተጨማሪ ፡ ቍ ፡ ፩ሺ፬፻፴፯ ፡ ስለ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ ሲናገር ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆነ፡ ድንጋጌ፡ ያደርጋል ።

በ፲፱ኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ሁለተኛ ፡ አጋማሽ ፡ ላይ ፡ አንዳንድ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግን ፡ አንድ ፡ የግዴታዎች ፡ ምንጭ ፡ እንዲሆንና ፡ አክሲዮ ፡ ደ ፡ ኤን ፡ ሬም ፡ ቬርሶ ፡ ተብሎ ፡ የታወቀውን ፡ ደግሞ ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ የክስ ፡ አርእስት፡ ለማድረግ ፡ ንቅናቄ ፡ ጀመሩ ። ከመሪዎቹም ፡ መካከል ፡ አብሪና ፡ ሮው ፡ ሲገኙ ፡ እነርሱም ፡ ፒይማ ፡ ደ ፡ ሊንዱና ፡ ኸርስቲዮን ፡ ዳፌር ፡ የተባሉትን ፡ እንደ ፡ ሁለት ፡ የአለአግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ምሳሌዎች ፡ ብቻ ፡ በመቁጠር ፤ ደ ፡ ኢንሬም ፡ ቬርሶ ፡ የተባለው ፡ ክስ ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ መጎዳት ፡ ምክንያት ፡ ያንድ ፡ ሰው ፡ ሃብት ፡ በዳበረ ፡

---

5. ጥላንዮል ፡ ኤ፡ ሪፔር ፡ ትሬቴ ፡ ፕራቲክ ፡ ደ ፡ ድርዋ ፡ ሲቪል ፡ ፍራንሴ ፡ (፪ኛ ፡ እትም ፡ በፒ- ኤስማን ቦልዩም ፡ ፯ ፡ ቍ ፡ ፯፻፶፪ ፡ ገጽ ፡ ፵፯ ።
6. ጥላንዮል ፡ ኤ ፡ ሪፔር ፡ ላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ የግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ (፫) ፡ እስከ ፡ ቍ ፡ ፯፻፶ ፡ ገጽ ፡ ፵፯፡ ድንጋጌዎቹ ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ፡ ይላሉ ፡- ቍጥር ፡ ፭፻፵፰ ፡ ፭፻፶፬-፭ ፡ ፭፻፷-፷፩ ፡ ፰፻፷፩-፷፪ ፡ ፩ሺ፫፻፵፩ ፡ ፩ሺ፫፻፹፩ ፡ ፩ሺ፮፻፸፫ ፡ ፩ሺ፬፻፴፯ ፡ ፩ሺ፭፻፷፪ ፡ ፩ሺ፰፻፹፬ ፡ ፩ሺ፱፻፵፯ ፡ ፪ሺ፹ ፡ ፪ሺ፩፻፪ ፡ (፫) ፡ ፪ሺ፩፻፸፭ ።
7. ኤ ፡ ኮሊን ፡ ኤ ፡ ኤች ፡ ካፒታ ፡ ኩር ፡ ኤሌሜንቴር ፡ ደ ፡ ድርዋ ፡ ሲቪል ፡ ፍራንሴ ፡ (፯ኛ ፡ እትም ፡ ፲፱፻፴፪ ፡ እ - ኤ- አ-) ቮልዩም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፪፻፴፫ ፡ ገጽ ፡ ፪፻፹፫-፪፻፹፬ ።

ቁጥር ፡ መስጠት ፡ የሚገባው ፡ የክስ ፡ አርእስት ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ አስተያየታቸውን ፡ አቅ ርበዋል ።[8] በመጀመሪያ ፡ የካሳሲዮን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይህን ፡ አሳብ ፡ ችላ ፡ ብሎት ፡ ቆየ ። ነገር ፡ ግን ፡ በ፲፰፻፸፫ ፡ ዥስትዮን ፡ ደፌር ፡ አኖርማል ፡ በተባለ ፡ አሳብ ፡ ላይ ፡ የተመረኮዘ ፡ ክስ ፡ በመፍቀዱ ፡ መጠን ፡ የኦብሪና ፡ ሮውን ፡ አስተያየት ፡ ተቀብሎ ታል ።[10]

ትንሽ ፡ ቆይቶ ፡ በተነሳ ፡ ጉዳይ ፡[11] የካሳስዮን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ያላግባብ ፡ መበል ጸግን ፡ የክስ ፡ አርእስት ፡ ለማድረግ ፡ ስላልፈለገ ፡ በተመሳሳይ ፡ ዘዴ ፡ ተጠቅሟል ። በቡድየር ፡ ጉዳይ ፡[12] ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እላይ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ዘዴ ፡ ትቶ ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግን ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ የግዴታዎች ፡ ምንጭ ፡ አደረገው ። በአብ ሪና ፡ ሮው ፡ አሳብ ፡ የተመራ ፡ ቢሆንም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ የሚለ ውን ፡ መሠረተ ፡ አሳብ ፡ የሰጠው ፡ ትርጓሜ ፡ እነርሱ ፡ ካቀረቡት ፡ የተለየ ፡ ነበር ።[13] ተከትለው ፡ በመጡ ፡ ሁለት ፡ ጉዳዮች ፡ ግን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የጸሐፊዎቹን ፡ እቅድ ፡ ተቀብሎታል ።[14]

በብሪያኖ ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ተገለጠው ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስ ፡ መቅረብ ፡ የሚችለው ፡ የሚከተሉት ፡ ተሟልተው ፡ ሲገኙ ፡ ነው ።

ሀ/ የተከሳሽ ፡ መበልጸግ ፡

ለ/ የከሳሽ ፡ ሃብት ፡ መቀነስ

ሐ/ በመበልጸጉና ፡ በሀብት ፡ መቀነሱ ፡ መካከል ፡ የአፈጻጸም ፡ ግንኙነት ፡ ሲኖር፡

መ/ ለመበልጸጉ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ አለመኖሩ ፡

ሠ) ከሳሽ ፡ በውል ፡ ወይም ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ በሚፈጠር ፡ ግዴታ ፡ ክስ ፡ ማቅ ረብ ፡ የማይችል ፡ በሚሆንበት ፡ ጊዜ ። የመጨረሻው ፡ ሁኔታ ፡ በጸሐፊዎች ፡ ዘንድ ፡ አክስዮ ፡ ደ ፡ ኢን፡ ሬም ፡ ቬርሶ፡ተብሎ ፡ የታወቀው ፡ ክስ ፡ የተከታይነት ፡ ደረጃ ፡ ብቻ ፡ እንዳለው ፡ የሚያሳይ ፡ ነው ፡ በሚል ፡ መንገድ ፡ ተተርጉሟል ።

በሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ይህ ፡ በክስ ፡ ረገድ ፡ የተከታይነት ፡ ደረጃ ፡ የሚለው ፡ አነ ጋገር ፡ በትክክል ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ለመወሰን ፡ እንሞክራለን ።

---

8. ማዞ ፡ ኤ ፡ ማዞ ፡ ላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ ቍ– ፲፱፻፶፬ ፡ ገጽ ፡ ፲፱፻፴፯ ።
9. ከዚያው ፡ ቍ– ፲፱፻፶፭ ፡ ገጽ ፡ ፲፱፻፴፯፡ በተጨማሪም ፡ ሮው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ክሱን ፡ እንዲፈቅድ ፡ ማስደረ ጉን ፡ ይናገራሉ ።
10. ከሳሽ ፡ ኮምዩን ፡ ደ ፡ ላን-ሺንያ ፡ ተከሳሽ ፡ ጉይ ፡ ዲ- ፩ሺ፰፻፸፫ ፡ ፩፬፻፶፯ ።
11. ከሳሽ ፡ ላሜር ፡ ተከሳሽ ፡ ሻምቦ ፡ ሲንዲክ ፡ ደ ፡ ላ ፡ ፊየት ፡ ላሙር ፡ ዲ- ፩ሺ፰፻፺፩- ፩፻፵፱ ፡ የፐላኖል ፡ ማስታወሻ ።
12. ከሳሽ ፡ ዡልያ ፡ ፖቱር- ሚራን ፡ ተከሳሽ ፡ ቡዲየ ፡ ዲ ፡ ፩ሺ፰፻፺፪- ፩ሺ፰፻፺፫ ፡ ስለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እርምጃ፡ መግለጫ ፡ ኒኮላስ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሰ ፡ እና ፡ ፐላንዮል ፡ ኤ ፡ ሪፔር ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሰ ፡ ቍ– ፲፱፻፶፪ ፡ ገጽ ፡ ፵፱ ፡ ይመለከታል ።
13. የጸሐፊው ፡ አሳብ ፡ አብሪ ፡ ኤ ፡ ሮው ፡ ኰር ፡ ደ ፡ ድሮዋ ፡ ሲቪል ፡ ፍራንሴ ፡ (፬ኛ ፡ እትም) ፡ ቍ– ፳፻፸፰ ውስጥ ፡ እንደተገለጠው፡ በኤፍ- ጉሬ ፡ ላንሪሽማ ፡ አ ፡ ዴፓንስ ፡ ዶትሩዊ ፡ (፲፱፻፵፱ ፡ እ- ኤ- አ-) 'ቍ- ፩፻፹፫ ገጽ ፡ ፩፻፹፰ ፡ ውስጥ ፡ ተጽፎአል ።
14. ከሳሽ ፡ ክላየት ፡ ተከሳሽ ፡ ሊኪ- ደ ፡ ላ ፡ ኮንግራጋሲዮ ፡ ደ ፡ ሚሲዮነር ፡ ደ ፡ ላስ ፡ ሳሌት ፡ ኤስ- ፩ሺ፱፻፲፰- ፩-፵፩ ፡ እና ፡ ከሳሽ ፡ ቪይ ፡ ደ ፡ ባኬር- ደ- ቢጐር ፡ ተከሳሽ ፡ ብሪያን ፡ ዲ- ፩ሺ፱፻፳- ፩-፩፻፪ ።
15. ፐላንዮል ፡ ኤ ፡ ሪፔር ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሰ ፡ ቍ– ፲፱፻፷፩ ፡ ገጽ ፡ ፷፯ ።

የፈረንሣይ ፡ ሕግ ፡ አላግባብ ፡ በመበልጸግ ፡ ምክንያት ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ ሁኔታዎች ፡ አብራርቶ ፡ ሲያስረዳ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ክሱ፡ የተከታይነት ፡ ወይም ፡ የሁለተኛ ፡ ደረጃነት ፡ ምንም ፡ ሳይጠቅስ ፡ በደፈናው ፡ ክሱ ፡ ሊቀርብ ፡ የሚችለው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በሌላው ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ ንብረት ፡ ምክንያት ፡ አላግባብ ፡ በሚበለጽግበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ይላል ።[16]

## ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ አርእስተ ፡ ክስ ፡ ተከታይነት ፡ ወይም ፡ የሁለተኛነት ፡ ደረጃ ፡ (ሳብሲዲያሪቲ) ፡

ይህ ፡ ጽሑፍ ፡ የሚናገረው ፡ ስላላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ አርእስተ ፡ ክስ ፡ ተከታይነት ፡ ደረጃ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። አስቀድመን ፡ ግን ፡ "ምክንያት" ስለሚባለው ፡ መሠረተ አሳብ ፡ ባጭሩ ፡ መናገር ፡ ይጠቅማል ። ለዚህም ፡ ሁለት ፡ ምክንያት ፡ አለው ። በመጀመሪያ ፡ በፈረንሳይ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የዚህን ፡ መሠረተ ፡ አሳብ ፡ ጉዳይ ፡ ስንመረምር በአንድ ፡ በኩል ፡ "ምክንያት" ከሚለው ፡ ጋር ፡ የተሳሰረ ፡ ሆኖ ፡ ስለምናገኘው ፡ ነው። ሁለተኛ ፡ ደግሞ ፡ ይህ ፡ "የተከታታይነት" ጉዳይ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ መኖር ፡ አለመኖሩን ፡ ለማወቅ ፡ "ምክንያት" ከሚባለው ፡ መሠረተ ፡ አሳብ ፡ መልሳችንን፡ ማግኘት፡ ስላለብን፡ ነው። በፈረንሣይ፡ ሕግ፡ ውስጥ፡ በሁለቱ ፡ መሠረተ፡ አሳቦች፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ መደራረብ ፡ ለመረዳትና ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ "የተከታይነት ፡ ወይም ፡ የሁለተኛነት ፡ ደረጃ" ፡ የሚለው ፡ መሠረተ ፡ አሳብ ፡ መኖር ፡ አለመኖሩን ፡ ለመመርመር ፡ ለአንድ ፡ ብልጽግና ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ለመሆን ፡ የሚችሉትን፡ ነገሮች ፡ ማወቅ ፡ ይኖርብናል ። ቀጥለንም ፡ በፈረንሣይ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ "ተከታይነት" ፡ እንዲሁም ፡ ይህ ፡ ንጥረ ፡ ሃሳብ ፡ ስለተፈጠረበት ፡ ምክንያትና ፡ በመጨረሻም በዚሁና ፡ በ"በቂ ፡ ምክንያት ፡" መካከል ፡ ስላለው ፡ መደራረብ ፡ እንነጋገራለን ።

፩/ "<u>በቂ ፡ ምክንያት ፡</u>"

በፕላንዮልና ፡ ሪፔር ፡ አስተያየት ፡—

"መበልጸግ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ የሚኖረው ፡ በውል ፡ መሠረት ፡ ወይም ፡ ከሕጋዊ ፡ ወይም ፡ ከተፈጥሮ ፡ ግዴታ ፡ የተገኘ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።"[17]

ስለዚህ ፡ በበለጸገው ፡ ወገንና ፡ ሃብቱ ፡ በተቀነሰበት ፡ ወገን ፡ መካከል ፡ ውል ፡ ሲኖርና ፡ ለዚሁ ፡ ሁኔታ ፡ ምክንያት ፡ ሁኖ ፡ ሲገኝ ፡ እንደ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ይቆጠራል ።

እንዲሁም ፡ የበለጸገው ፡ ወገን ፡ ከአንድ ፡ ካለ ፡ ምክንያት ፡ ከበለጸገ ፡ ሰው ፡ ጋር፡ ሲዋዋልና ፡ ይኸው ፡ ሰው ፡ ውሉን ፡ ለመፈጸም ፡ የበቃው ፡ ካለምክንያት ፡ ባገኘው ፡ ብልጽግና ፡ ቢሆንም ፡ ውሉ ፡ በደንቡ ፡ መሠረት ፡ ተዋውሎ ፡ የበለጸገው ፡ ወገን ፡ ላገኘው ፡ ብልጽግና ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ይሆናል ።[18] ጸሐፊዎቹ ፡ ይኸንን ፡ ሁኔታ ፡ በም

16. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍ ፡ ፪ሺ፩፻፷፪ ።
17. ፕላንዮል ፡ ኤ ፡ ሪፔር ፡ <u>ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሰ</u> ፡ ቍ ፡ ፯፻፶፯ ፡ ገጽ ፡ ፶፯ ።
18. <u>ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሰ</u> ፡ ቍ ፡ ፯፻፶፱ ፡ ገጽ ፡ ፷፩ ።

ሳሌ ፡ ሲያስረዱ ፡ የሚከተለውን ፡ የፍርድ ፡ ጉዳይ[19] ይጠቅሳሉ ። አንድ ፡ ቤት ፡ የተ ከራየ ፡ ሰው ፡ ሰራተኛ ፡ ቀጥሮ ፡ ቤቱን ፡ አሳደሰ ። በኪራዩ ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ ተከራዩ ፡ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ስለሚያደርገው ፡ መሻሻል ፡ አከራዩ ፡ ምንም ፡ እንደማይከፍለው፡ተጠ ቅሶ ፡ ስለነበረ ፡ ሠራተኛው ፡ ተከራዩ ፡ ሳይከፍለው ፡ የቀረውን ፡ ገንዘብ ፡ አከራይን፡ ከሶ ፡ ቢጠይቅ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጥያቄውን ፡ ሳይቀበለው ፡ ቀረ ።

እንዲሁም ፡ ያንድ ፡ ሰው ፡ መበልጸግ ፡ የተገኘው ፡ በሌላው ፡ ቸርነት ፡ ወይም ፡ የተፈጥሮ ፡ ግዴታ ፡ መፈጸም ፡ ከሆነ ፡ ሃብቱ ፡ የተቀነሰበት ፡ ወገን ፡ አክስዮ ፡ ደ ፡ ኢን ፡ ሬም ፡ ቬርሶ ፡ የተባለውን ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ አይችልም ።[21]

በመጨረሻም ፡ የመበልጸግ ፡ ምንጭ ፡ ሕግ ፡ ይሆናል ። አንድ ፡ ሰው ፡ ሕግ ፡ የሚ ያዘውን ፡ ግዴታ ፡ በሚፈጽምበት ፡ ጊዜ ፡ የበለጸገው ፡ ወገን ፡ አለ ፡ በቂ ፡ ምክንያት፡ በልጽጓል ፡ አይባልም ።[22]

ሌሎች ፡ ጸሐፊዎች ፡ ፕላንዮልና ፡ ሪፔር ፡ ከጠቀሷቸው ፡ ምንጮች ፡ ሌላ ፡ ስለማ ይጠቅሱና ፡ አስተያየታቸውም ፡ ከነዚሁ ፡ ጸሐፊዎች ፡ በምንም ፡ ያህል ፡ ስለማይለ ያይ ፡ መዘርዘሩ ፡ አስፈላጊ ፡ አይሆንም ።[23]

፪ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ አርእስተ ፡ ክስ ፡ የተከታይነት ፡ ጠባይ ።

ከሳሹ ፡ ሊከስበት ፡ የሚችል ፡ ሌላ ፡ መንገድ ፡ እንዲኖረው ፡ አይገባም ፡ የሚ ለው ፡ አነጋገር ፡ ብዙ ፡ ትርጓሜ ፡ ሊሰጠው ፡ ይችላል ። ለምሳሌ ፡ ባርተን ፡ ሊሰጡት ፡ ስለሚችሉት ፡ ትርጓሜዎች ፡ የሚከተለውን ፡ አስተያየት ፡ ይሰጣል ።

"የተከታይነት ፡ ጠባይ ፡ በሶስት ፡ ሊተረጎም ፡ ይችላል ። በመጀመሪያ ፡ ከሳሽ ፡ ይህን ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ የሚችለው ፡ ተከሳሹ ፡ የበለጸገበት ፡ ሁኔታ ፡ በተከሳሹ ፡ ሆነ ፡ በሌላ ፡ ሶስተኛ ፡ ወገን ፡ ላይ ፡ ሌላ ፡ ዓይነት ፡ ክስ ፡ ሊቀርብበት ፡ የማይችል ፡ ሲሆን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መተርጎም ፡ ይቻላል ። ሁለተኛ ፡ ከሳሹ ፡ ሌላ ፡ ክስ ፡ መመስረት ፡ ሲችል ፡ ይህን ፡ ሳይፈጽም ፡ በመቅረቱ ፡ የክስ ፡ ማቅረብ ፡ ችሎታውን ፡ ሲያጣ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። ሶስተኛ ፡ ደግሞ ፡ ሊያቀርብ ፡ ይችል ፡ የነበረው ፡ ሌላው ፡ ክስ ፡ ክሱ ፡ ሊቀርብበት ፡ ይቻል ፡ የነበረው ፡ ሰው ፡ በመክሰሩ ፡ ምክንያት ፡ የማይጠቅም ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መተርጎምም ፡ ይቻላል ።"

እነዚህንና ፡ እነሱን ፡ የመሳሰሉትን ፡ ጥርጣሬዎች ፡ ለማስወገድና ፡ "የተከታይ ነት ፡ ጠባይ ፡" የተባለው ፡ ሁኔታ ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ለመወሰን ፡ አራት ፡ የተለያዩ ፡ የፍርድ ፡ ጉዳዮችን ፡ በመውሰድ ፡ በአንድ ፡ በኩል ፡ የሕግ ፡ ደራስያን ፡ የሚያቀርቡ ትን ፡ መፍትሔ ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ለነዚህ ፡ ጉዳዮች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የሰጡ ትን ፡ ውሳኔ ፡ እንመረምራለን ።[24]

---

19. ከሳሽ ፡ ሄርቤር ፡ ተከሳሽ ፡ ቧይ ፡ ሃርዲ ፡ ኤ ፡ ሻንስ ፡ ዲ ፡ ፩ሺ፱፻- ፪-፩፻፶፬ ።

20. ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ ቍ ፡ ፯፻፰ ፡ ገጽ ፡ ፰፫-፰፬ ።

21. ከዚያው ።

22. ለምሳሌ ፡ ማዞ ፡ ኤ ፡ ማዞን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሰ ፡ ቍ- ፯፻፪—፯፶፭ ፡ ገጽ ፡ ፯፻፵-፯፻፵፩ ፤ ኮሊ ፡ ኤ፡ ካፒታ ፡ ትሬቴ ፡ ደ ፡ ድርዋ ፡ ሲቪል ፡ (፲፱፻፶፱ ፡ እ- ኤ- አ-) ፡ ቮልዩም ፡ ፪ ፡ ቍ- ፩ሺ፫፻፷፩-፩ሺ፫፻፷፫ ፡ ገጽ ፡ ፯፻፵፱- ፯፻፶ ።

23. ማስታወሻ ፡ ቍ- ፲ ፡ ገጽ ፡ ፫፻፷፩ ፡ አንቀጽ ፡ ፭፻፸፰ ፡ በኦብሪ ፡ ኤ ፡ ሮው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሰ፡ (፭ኛ ፡ እትም ፡) ቮልዩም ፡ ፱ ፡ ውስጥ ፤ በቻሊስ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሰ ፡ ውስጥ ፡ ገጽ ፡ ፩፻፰ ፡ላይ ፡ የተጠቀሰ ።

፩/ ከሳሹ ፡ ሌላ ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ ይችል ፡ ነበር ፡ አሁን ፡ ግን ፡ ሕጉ ፡ ዕንቅፋት ፡ ስለሆነበት ፡ ማለትም ፡ አንድ ፡ የሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ስለሚከለክለው ፡ ያንን ፡ ክስ ፡ ሊያቀርብ ፡ አይችልም ፡ በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ደ ፡ ኢን ፡ ሬሞ ፡ ቬርሶ ፡ የተባለውን ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ ይችላልን ? ለምሳሌ ፡ ከሳሽ ፡ በውል ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ክስ ፡ ሊያቀርብ ፡ ይችል ፡ ነበር፤ነገር፡ግን፡ሕጉ፡ በሚያዘው፡ጊዜ፡ውስጥ፡ክሱን ፡ ስላላቀረበ፡ በይርጋ ፡ ይታገዳል።

ጸሐፊዎች ፡ ሁሉ ፡ በአንድ ፡ ድምጽ ፡ በእንደዚህ ፡ ዓይነት ፡ ሁኔታ ፡ ደ ፡ ኢን ፡ ሬም ፡ ቬርሶ ፡ የተባለውን ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ አይቻልም ፡ ይላሉ ። ለዚህም ፡ የሚሰጡት ምክንያት ፡ ይህ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በጊዜው ፡ ያለውን ፡ የሕግ ፡ ሥርዓት ፡ ማናወጽ ፡ ይሆናል ፡ የሚል ፡ ነው ።[25] የሚከተሉት ፡ ከፕላንዮልና ፡ ሪፔር ፡ እንዲሁም ፡ ከማዞና ፡ ማዞ ፡ የተውጣጡ ፡ አጫጭር ፡ ንባቦች ፡ የሕግ ፡ ደራሲያን ፡ ዓይነተኛ ፡ አስተያየቶች ፡ ናቸው ።

ፕላንዮናልና ፡ ሪፔር ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ ዓይነት ፡ ክስ ፡ በሕግ ፡ በታገደ ፡ ጊዜ ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስ ፡ ሲቀርብ ፡ አንቀበልም ፡ ያሉትን ፡ በመደገፍ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ያለውን ፡ አስተያየት ፡ ያበረክታሉ ።

ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በሕግ ፡ በታገደ ፡ ክስ ፡ ፈንታ ፡ ደ ፡ ኢን ፡ ሬም፡ ቬርሶ ፡ ክስ ፡ መተካት ፡ አይችልም ፡ ያሉበት ፡ ግልጽ ፡ ምክንያት ፡ ክሱን ፡ መቀበል ፡ ስለ ፡ ማስረጃ ፡ ስለ ፡ ይርጋ ፡ ስለ ፡ መብት ፡ መቅረትና ፡ እንዲሁም ፡ ስለ ፡ ክስ ፡ ፍጻሜነት ፡ ያሉንን ፡ ሕጎች ፡ እንደማፍረስ ፡ ስለሚቆጠር ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ሕጎች ፡ ያንዱን ፡ ወገን ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ የሚያጸድቁ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ በተዘዋዋሪ ፡ መንገድ ፡ መፍረስ ፡ የለባቸውም ። ለምሳሌ ፡ አንድ ፡ ተበዳሪ ፡ የተበደረውን ፡ ገንዘብ ፡ ባለመመለሱ ፡ ያላግባብ ፡ በልጽጓልና ፡ በይርጋ ፡ ምክንያት ፡ ከብድሩ ፡ ነፃ ፡ አይሆንም ፡ ማለት ፡ አይገባም ፡ ስለ ፡ ይርጋ ፡ ስለ ፡ ጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ የተደነገገውን ፡ ሕግ ፡ መሻር ፡ ይቻላል ። ነገር፡ ግን ፡ በአክስዮ ፡ ደ ፡ ኢን ፡ ሬም ፡ ቬርሶ ፡ አማካይነት ፡ እነዚህን ፡ ሕጎች ፡ መሻር ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ ሸፍጥ ፡ እንደመፈጸም ፡ የሚቆጠር ፡ ነው ።[26]

እንደ ፡ ፕላንዮልና ፡ ሪፔር ፡ በጠቅላላ ፡ በነዚህ ፡ ሁኔታዎች ፡ አላግባብ ፡ መበልጸግን ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ የሚቀርበውን ፡ ክስ ፡ ሳያወግዙ ፡ ማዞና ፡ ማዞ ፡ እያንዳንዱን ፡ ሁኔታ ፡ ለብቻው ፡ በመመርመር ፡ ሕጉ ፡ ሌላ ፡ ክስ ፡ የሚከለክልባቸውን ፡ ሁኔታዎች ፡ ያጠናሉ ። እነርሱም ፡ "ሕጉ ፡ ለከሳሹ ፡ የፈቀደለት ፡ ሌላ ፡ የክስ ፡ አርእስት በይርጋ ፡ ሲታገድ ፡ የደ ፡ ኢን ፡ ሬም ፡ ቬርሶ ፡ ክስ ፡ እንዲቀርብ ፡ መፍቀድ ፡ አይቻልም ። ከዚህ ፡ የተቃረነ ፡ አስተያየት ፡ የይርጋን ፡ ሕግ ፡ ጨርሶ ፡ እንደማውደም ፡ የሚቆጠር ፡ ነው ። ይህንኑ ፡ አስተሳሰብ ፡ በመከተል ፡ የደ ፡ ኢን ፡ ሬም ፡ ቬርሶ ፡ ክስ ፡ ስለ ፡ ረጅም ፡ ይዞታ ፡ የተደነገገውን ፡ ወይም ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፲፱ ፡ የተመለከተውን ፡ ሕግ ፡ ውጤት ፡ በሚያሳጣው ፡ ዓይነት ፡ ሊጠቀምበት፡አይቻልም፡" ብለው ፡ ጽፈዋል ። አሁን ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በተለይም ፡ የካሳስዮን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ጉዳይ ፡ ሲያጋጥመው ፡ የሰጣቸውን ፡ ውሳኔዎች ፡ እንመልከት ።

---

24. ይህ ፡ ብዙ ፡ ጸሐፊዎች ፡ የሚጠቀሙበት ፡ አስተሳሰብ ፡ ነው ፡ ለምሳሌ ፡ ማዞና ፡ ማዞ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርእስት ፡ ቍ ፡ ፲፻፺-፲፻፱ ፡ ገጽ ፡ ፲፻፵፱-፲፻፶፫ ፡ ተመልከት ።
25. ቻሊስ ፡ ላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ገጽ ፡ ፩፻፳፰ ።
26. ፕላኒዮልና ፡ ሪፔር ፡ ላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ቍ- ፲፻፷፩ ፡ ገጽ ፡ ፰፯ ፡
27. ማዞና ፡ ማዞ ፡ ላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ አርእስት ፡ ቁ ፡ ፲፻፷ ገጽ ፡ ፲፻፵፫ ፡

አላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስ ፡ በሌላ ፡ በሕግ ፡ በታገደ ፡ ክስ ፡ ምትክ ፡ ተተክቶ ፡ ሲቀርብ ፡ ተቀባይነት ፡ አይኖረውም ፡ የሚሉ ፡ ብዙ ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔዎች ፡ አሉ ።[28]

በክላየት ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ የከሳሿን ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሳይቀበለው ፡ የቀረው ፡ ክሱን ፡ መፍቀድ ፡ ከሳሿ ፡ በመጀመሪያ ፡ በብድር ፡ ውል ፡ ላይ ያቀረበችውን ፡ ክስ ፡ ያገዱትን ፡ ቍ. ፩ሺ፫፻፵፩ ፡ እና ፡ ቍ. ፩፻፫፻፵፯ ፡ እንደ ፡ መሻር ፡ የሚቆጠር ፡ ሆኖ ፡ በመገኘቱ ፡ ነው ።

እንዲሁም ፡ በብሪያኖ ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ ከሳሹ ፡ ባላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተውን ፡ ክስ ፡ ያቀረበው ፡ ቍ. ፩ሺ፯፻፺፫ ፡ የሚያዘውን ፡ ለመፈጸም ፡ ባለመ ቻሉ ፡ ስለሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሳይቀበለው ፡ ቀርቷል ። ይህንኑ ፡ የሚመስለው ፡ ጉዳይ በከሳሽ ፡ በደሚዜል ፡ ደጉስት ፡ ደ ፡ ሲንስሲኒና ፡ በተከሳሽ ፡ በግሩምባህ ፡ ኤ ፡ ኮምፓኚ ፡[29] የቀረበው ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። ከሳሽ ፡ ክሱን ፡ ያቀረበችው ፡ የጠፋባትን ፡ የጌጣ ጌጥ ፡ ማስቀመጫ ፡ ለማስመለስ ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ ለያዘው ፡ ሰው ፡ ፲፯ሺ ፡ ፍራንክ ፡ ስለከፈለች ፤ ዕቃውን ፡ ከሸጠው ፡ ሰው ፡ በአላግባብ ፡ በመበልጸግ ፡ ክስ ፡ መሠረት ፡ የከፈለችው ፡ እንዲመልስላት ፡ ለማድረግ ፡ ነበር ። ሻጩ ፡ ዕቃውን ፡ የገዛው ፡ ከሌባ ፡ ላይ ፡ ነበር ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከሳሿ ፡ በቍ. ፪ሺ፪፻፸፱ ፡ እና ፡ በቍ. ፪ሺ፪፻፹ ፡ መሠረት፡ ነጋዴው ፡ ዕቃውን ፡ ሲገዛ ፡ ጥፋት ፡ ማድረጉን ፡ ለማስረዳት ፡ አትችልም ፡ የሚል ፡ ግምት ፡ ስለገባው ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግን ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ በኩባንያው ፡ ላይ ፡ ያቀረበችውን ፡ ክስ ፡ ውድቅ ፡ አደረገው ።

፪/ ከሳሹ ፡ ሌላ ፡ ክስ ፡ ሊያቀርብ ፡ ይችል ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በራሱ ፡ ጥፋት ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ስላጓደለ ፡ ክሱን ፡ ከማቅረብ ፡ ታግዷል ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ በአላግባብ፡ መበ ልጸግ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ክስ ፡ ሊያቀርብ ፡ ይችላልን ? የመጀመሪያውን ፡ ክስ ፡ ከማቅረብ ፡ የታገደው ፡ ሕጉ ፡ የሚያዘውን ፡ ባለማወቁ ፡ ወይም ፡ በቸልተኝነት ፡ ምክንያት ፡ ባለመፈጸሙ ፡ ነው ።[30] ይህ ፡ ሲሆን ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስ ፡ በታገደው ፡ ክስ ፡ ምትክ ፡ ሊተካ ፡ ይችላል ፡ የሚል ፡ ማንንም ፡ ጸሐፊ ፡ አላገኘንም ። ፕላንዮልና ፡ ሪፔር ፡ በሕግ ፡ እክልና ፡ በከሳሹ ፡ ቀጥታዊ ፡ ምክንያት ፡ በሚፈጠር ፡ እክል ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ አያደርጉም ፤ ሁለቱንም ፡ ዓይነት ፡ እክሎች ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ ሽፍጥ ፡ ማስከተል ፡ አይገባቸውም ፡ በሚል ፡ መስመር ፡ ስለሚመለከቷቸው ፡ እንደ ሚከተለው ፡ ይጽፋሉ ፡—

አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ያንድ ፡ ወገን ፡ መበልጸግና ፡ የሌላው ፡ ወገን ፡ መደህየት ፡ የተ ያያዙ ፡ ቢሆኑም ፡ አንድ ፡ የሕግ ፡ አንቀጽ ፡ የካሣ ፡ መክፈሉን ፡ ጉዳይ ፡ የሚያግድ ፡

28. ፕላኒዮልና ፡ ሪፔር ፡ ላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ቍ ፸፯ ፡ ገጽ ፡ ፷፯ ፡ የግርጌ ፡ ማስረጃ ፡ (፩) ፡ (፫-፯) ፡ ገጽ ፡ ፷፯ ፡ የግርጌ ፡ ማስረጃ ፡

29. (፩—፫) ዲ- ፒ ፲፱፻፵፩ - ፩ - ፩፻፭፱

30. በተጨማሪም ፡ ያልታወቀና ፡ ያልተገመተ ፡ ስህተት ፡ ባንዳንድ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ይጨመራል ። የሚከተሉት ፡ ጸሐፊዎች ፡ ደ ፡ ኢን ፡ ሬም ፡ ቨርሶ ፡ ክስ ፡ በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ ይፈቅዳሉ ። ቻሊስ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ገጽ ፡ ፩፻፳፩ ፤ ኮለንና ፡ ካፒታ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ (፩ኛ ፡ እትም) ፡ ቮልዩም ፡ ፪ ፡ ገጽ ፡ ፩፻፲፯ ፤ ዦስራ ፡ ኰር ፡ ደ ፡ ድርዋ ፡ ሲቪል ፡ ፓሲቲፍ ፡ ፍራንሴ ፡ (፪ኛ ፡ እትም) ፡ ቮልዩም ፡ ፪ ፡ ቍጥር ፡ ፩፻፵፯ ፡ ገጽ ፡ ፫፻፲፯ ፤ ሪፔር ፡ ላ ፡ ሬግል ፡ ሞራል ፡ (፪ኛ ፡ እትም) ፤ ገጽ ፡ ፩፻፶ ። በመጻሕፍት ፡ ቤታችን ፡ የሚገኘው ፡ የሪፔር ፡ መጽሐፍ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የሚናገረው ፡ ስለ ውል ፡ መፍረስ ፡ ወይም ፡ መለወጥ ፡ ስለሆነ ፡ የቻሊስን ፡ "የማይገመት ፡ ስህተት" ከጽሑፌ ፡ አስወግጀዋለሁ ።

መሆን ፡ አለመሆኑን ፡ መወሰን ፡ ያዳግታል ። ለምሳሌ ፡ ከሳሹ ፡ ላንድ ፡ ሰው ፡ ዕቃ ፡ ይሰጥና ፡ ዋጋውን ፡ ወደፊት ፡ እንዲከፍል ፡ ይዋዋላል ። ነገር ፡ ግን ፡ ከሌሎች ፡ ባለገንዘቦች ፡ ቅድሚያ ፡ የሚያሰጠውን ፡ መያዣ ፡ መጠየቅ ፡ ሲችል ፡ ሳይጠይቅ ፡ ይቀራል። ስለዚህም ፡ ከሌሎች ፡ ባለገንዘቦች ፡ ጋር ፡ ያለው ፡ መብት ፡ እኩል ፡ ወይም ፡ ያነሰ ፡ ይሆናል ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ በአከፋፈል ፡ አንድ ፡ ባለገንዘብ ፡ ከሌሎች ፡ ባለገንዘቦች ፡ ቅድሚያ ፡ ሊያሰጡት ፡ የሚችሉትን ፡ ፎርማሊቴዎች ፡ ካላሟላ ፡ በስተቀር ፡ ቅድሚያ አይሰጠውም ፡ የሚለው ፡ ሕግ ፡ ሰውየው ፡ ምንም ፡ ሌሎቹን ፡ ባለገንዘቦች ፡ በራሱ ፡ ጥፋት ፡ ምክንያት ፡ ቢጠቅማቸውም ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግን ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ ክስ ፡ እንዳያቀርብ ፡ አይከለክለውምን ? መልሱ ፡ ይከለክለዋል ፡ የሚል ፡ መሆን፡ አለበት ፡ እንላለን ።[31] ማርቲና ፡ ሬኖም ፡ ይህንኑ ፡ አስተያየት ፡ ይደግፋሉ ። እነርሱም ፡ "የሚገባው ፡ የክስ ፡ መንገድ ፡ በሕግ ፡ የታገደ ፡ ሲሆን ፡ ደ ፡ ኢን ፡ ሬም፡ ቬርስ፡ ክስ ፡ ሊተካው ፡ አይችልም ። ለምሳሌ ፡ ሕጉ ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ መያዣ ፡ የሆነውን ፡ ንብረት ፡ ሳያስመዘግብ ፡ሲቀር ፡ በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ ከርሱ ፡ መብት ፡ ጋር ፡ የተስተካከለ ፡ መብት ፡ የሚኖራቸውን ፡ ሌሎች ፡ አበዳሪዎች ፡ አላግባብ ፡ ተጠቅመዋል ፡ ብሎ ፡ ሊከስ ፡ አይችልም ።"[32] ይላሉ ፡ (ዲ - ፩ሺ፱፻፷፬ ፡ ፩ሺ፩፻፷፱)

ሩዋስት ፡ ደግሞ ፡ ጉዳዩን ፡ እንደሚከተለው ፡ አድርጎ ፡ አሳምሮ ፡ ገልጾታል ። በራሱ ፡ ጥፋት ፡ ምክንያት ፡ ማዕበል ፡ ውስጥ ፡ ለገባ፡ ሰው ፡ የደ ፡ ኢን ፡ ሬም ፡ ቬርሶ ፡ ክስ ፡ ማምለጫ ፡ ጀልባ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።[33]

አንድ ፡ ሰው ፡ ሊያቀርብ ፡ ይችል ፡ የነበረውን ፡ ክስ ፡ በገዛ ፡ ጥፋቱ ፡ ምክንያት ፡ ማቅረብ ፡ ሲያቅተው ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግን ፡ አርእስተ ፡ ክስ ፡ አድርጎ ፡ የሚያቀርበውን ፡ ክስ ፡ ውድቅ ፡ ያደረጉ ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔዎች ፡ አሉ ።[34] ከነዚህም ፡ አንዱ ፡ በ፩ሺ፱፻፷፬ ፡ የተወሰነው ፡ ነው ። በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ ከሳሹ ፡ በመሬቱ ፡ ላይ ፡ የልጁ ፡ ባል ፡ ቤት ፡ እንዲሠራ ፡ ገንዘብ ፡ አበደረው ። ቤቱ ፡ ተሰርቶ ፡ ሲያልቅ ፡ የከሳሹ ፡ ልጅ ፡ ባል ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ስለገባ ፡ ቤቱንም ፡ መሬቱንም ፡ መዋጮ ፡ አደረገው ። ከጊዜ ፡ በኋላ ፡ ማኅበሩ ፡ ከሰረና ፡ ሂሳብ ፡ ተጣራ ። ባላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ በተመሠረተ ፡ ክስ ፡ ከሳሹ ፡ ሌሎቹን ፡ የማኅበሩን ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ከሰሳቸው ። ክርክሩም ፡ የመሬቱ ፡ ዋጋ ፡ ጨምሯል ፡ ይህም ፡ ሊሆን ፡ የቻለው ፡ ለልጄ ፡ ባል ፡ ገንዘብ፡ አበድሬው ፡ በዚህ ፡ ገንዘብ ፡ መሬቱ ፡ ላይ ፡ ቤት ፡ ስለሰራበት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ የመሬቱ ፡ ዋጋ ፡ ጭማሪ ፡ በቅድሚያ ፡ ለኔ ፡ መከፈል ፡ አለበት ፡ ከሌሎቹ ፡ ጋር ፡ እኩል ፡ መብት ፡ የተሰጠኝ ፡ እንደሆን ፡ ግን ፡ እነሱ ፡ ያላግባብ ፡ በለጸጉ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ነበር ። ቍ ፡ ፪ሺ፩፻፫ ፡ (፬) ፡ እና ፡ (፩) ፡ በሚያዙት ፡ መሠረት ፡ የቅድሚያ ፡ መብት ፡ ይዞ ፡ ባለመቆየቱ ፡ የከሳሹ ፡ ክስ ፡ ውድቅ ፡ ሆነ ።

---

31. ፐላኒዮልና ፡ ሪፔር ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርእስት ፡ ቍ ፲፱፻፷፪ ፡ ገጽ ፡ ፷፰ ፡
32. ማርቲና ፡ ሬይኖ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርእስት ፡ ቍ ፡ ፫፻፶፫ ፡ (፪) ፡ ገጽ ፡ ፫፻፷-፴፪ ፡
33. ሩዋስ ፡ ላንሪሽስማ ፡ ሳን ፡ ኮዝ ፡ ኤ ፡ ላ ፡ ዡሪስፕሩዳንስ ፡ ሲቪል "ሬቩ ትሪሜስቴል ፡ ድሩዋ ፡ ሲቪል፡" ፲፱፻፷፪ ገጽ ፡ ፹፯ ፡ ድራኪዲስ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርእስት ፡ ገጽ ፡ ፳፻፹፩
34. ከሳሽ ፡ ክሬዲ ፡ ፎንሲየር ፡ ዶ ፡ ፍራንስ ፡ ተከሳሽ ፡ አራዘ ፡ ዲ ፡ ፩ሺ፷፻፹፱- ፩-፫፻፶፫ ፤ ከሳሽ ፡ ዣክ ፡ ተከሳሽ ፡ ላቤል ፡ ፍሬር ፡ ኤ ፡ ቤርቲኖ ፡ ዠን ፡ ዴ ፡ ፲፱፻፲፫ - ፩ሺ፬፻፴፫ ፡ በተጨማሪ ፡ በሌሎች ፡ የሕግ ጉዳይ ፡ ማከማቻ ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ ፡ ይገኛሉ ።
35. ከሳሽ ፡ ሎሬንስ ፡ ሲንዲክ ፡ ደ ፡ ላ ፡ ፋዪት ፡ ሶሲያል ፡ ሚፐል ፡ ኤ ፡ ታራይር ፤ ተከሳሽ ፡ ማርትይ ፡ ዲ ፡ ፒ ፡ ፲፱፻፷፬ ፡ ፩ - ፩፻፷፱ ፡

፫/ ከሳሹ ፡ ሌላ ፡ ክስ ፡ ሊያቀርብ ፡ ሲችል ፡ በራሱ ፡ ጥፋት ፡ ባልሆነ ፡ ምክንያት ፡ ክሱን ፡ ማቅረብ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ይሆናል ። ይህ ፡ የሚነሳው ፡ አንዱ ፡ ተዋዋይ ፡ ወገን ፡ ቢከስርና ፡ በውል ፡ የተመሠረተ ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ በማይጠቅምበት ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ።[36] ስለዚህም ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስ ፡ የሚቀርበው ፡ በሌላ ፡ በሶስ ተኛ ፡ ወገን ፡ ላይ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ክስ ፡ ሊቀርብ ፡ ይችላልን ?

ቁጥራቸው ፡ በጣም ፡ ትንሽ ፡ ከሆነ ፡ ጸሐፊዎች ፡ በስተቀር ፡ ጸሐፊዎች ፡ በእንደ ዚህ ፡ ዓይነት ፡ ሁኔታ ፡ ሁለተኛ ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ ይቻላል ፡ ይላሉ ። ይህ፡ሁኔታ ፡ ከላይ፡ ከተጠቀሱትና ፡ ወደፊት ፡ ከሚጠቀሱት ፡ ሁኔታዎች ፡ የሚለየው ፡ ባላግባብ ፡ መበል ጸግ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተው ፡ ክስና ፡ በውል ፡ የሚመሠረተው ፡ ክስ ፡ የሚመለከቱት ፡ ሁለት ፡ የተለያዩ ፡ ወገኖችን ፡ በመሆኑ ፡ ነው ። በተጨማሪ ፡ ሁለተኛው ፡ ክስ ፡ ሊተካ የሚችለው ፡ ሶስተኛው ፡ ወገን ፡ የበለጸገው ፡ አለ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ሲሆን ፡ ብቻ ፡ መሆኑን ፡ መዘንጋት ፡ አይገባም ። ፕላንዮልና ፡ ሪፔር ፡[37] እንደሚያመለክቱት ፡ የሶስ ተኛው ፡ ወገን ፡ መበልጸግ ፡ ከከሳሽ ፡ ሃብት ፡ መቀነስ ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ ቢሆንም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ውድቅ ፡ ይሆናል ። ምክንያቱም ፡ የሶስተኛው ፡ ወገን ፡ መበልጸግ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ስለሚኖረው ፡ ነው ።

ነገር ፡ ግን ፡ የበለጸገው ፡ ወገን ፡ ለብልጽግናው ፡ ምክንያት ፡ የሌለው ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ያልተከፈለው፡ ወገን፡ የደ፡ ኢን፡ ሬም ፡ ቬርሶ ፡ ክስ፡ ማቅረብ፡ ይችላል ። ምክንያቱም ፡ እንደዚህ ፡ ዓይነት ፡ ሁኔታ ፡ ሲያጋጥም ፡ ክሱን ፡ መፍቀድ ፡ ሕጉ ፡ የከለከለውን ፡ በተዘዋዋሪ ፡ መንገድ ፡ ማግኘትን ፡ ስለማያስከትል ፡ ነው ። ማለ ትም ፡ ጥቅም ፡ አይሰጥም ፡ እንጂ ፡ በውል ፡ የተመሠረተው ፡ ክስ ፡ አሁንም ፡ ሊቀ ርብ ፡ ስለሚችል ፡ ነው ።

ድራኪድስም ፡[38] ቢሆን ፡ ፍትሕ ፡ ስለሚፈቅደውና ፡ የክሱ ፡ ተተክቶ ፡ መቅረብ፡ የሕጉን ፡ አቋም ፡ ስለማያናጋ ፡ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ክስ ፡ እንዲቀርብ ፡ መፈቀድ፡ አለበት፡ ይላል ።

ሼቫልየር ፡[39] ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስ፡ መከልከል ፡ ያለበት፡ ሕግን ፡ የመሸሽያ ፡ ዘዴ ፡ ብቻ ፡ ሲሆን ፡ ነው ፡ ባይ ፡ ስለሆነ ፡ ባሁኑ ፡ ሁኔታ ፡ የክሱ ፡ መፈቀድ ፡ ተገቢ ፡ ነው ፡ ይላል ፡ "በውል ፡ የተመሠረተው ፡ ክስ ፡ በሁለተኛው ፡ ተዋዋይ ፡ መክሰር ፡ ምክንያት ፡ ብቻ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ሲሆን ፡ ነው ፡ ሶስተኛውን ፡ ወገን ፡ በመክሰስ ፡ ያላግባብ ፡ የያዘውን ፡ ሃብት ፡ እንዲመልስ ፡ ማድረግ ፡ የሚቻል" ፡ ሲል ፡ አትቷል ።

ኤስማይን ፡[40] ባንድ ፡ የካስሰዮን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ጉዳይ ፡ ቀርቦ ለት ፡ በሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ላይ ፡ አስተያየቱን ፡ ሲሰጥ "ይህ ፡ ክስ ፡ በሶስተኛ ፡ ወገን ፡ ላይ ፡ በመቅረቡ ፡ ከሳሹ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ሕግ ፡ ስላልተላለፈ ፡ የደ ፡ ኢን ፡ ሬም ፡ ቬርሶ ፡ ክስ ፡ የሚታገድበት ፡ ምክንያት ፡ የለም ፡" ብሏል ።

36. ማርቲና ፡ ሬይኖ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርእስት ፡ ፫፻፶፫ ፡ (፪) ገጽ ፡ ፫፻፷፩
37. ፕላኒዮልና ፡ ሪፔር ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ቍ ፡ ፯፻፷፫ ፡ (፪) ገጽ ፡ ፸፪ ፡
38. ድራኪዲስ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ገጽ ፡ ፭፻፹፯
39. ጂ ፡ ሼቫልዬ ፡ "አብዘርቫሲዮን ፡ ሱር ፡ ላ ፡ ሪፔቲስዮን ፡ ዴዘንሪሽማን ፡ ኖን ፡ ኮዜ" ለ ፡ ድሩዋ ፡ ፕሬቬ ፡ አ ፡ ሚሊየ ፡ ዲዩ ፡ በንቲየም ፡ ሲየክል ፡ (፲፱፻፶፱) ፡ ቮልዩም ፪ ገጽ ፡ ፪ ፡ ፪፻፵፰
40. በግርጌ ፡ ማስረጃ ፡ ቍጥር ፡ ፩፻፹፩ ፡ ጉሬ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ገጽ ፡ ፩፻፹፭ ፡ የቀረበ ።

አብዛኞቹ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ከሚሰጡት ፡ አስተያየት ፡ በመለየት ፡ ጎሬ ፡ በንደዚህ ፡ ዓይነት ፡ ሁኔታ ፡ ክሱን ፡ መፍቀድ ፡ ሕጉን፡መተላለፍን ፡ ስለሚያስከትል ፡ መፈቀድ ፡ የለበትም ፡ ይላል ። አስተሳሰቡ ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።[41] ተተኪውን ፡ ክስ ፡ መፍቀድ ፡ ከሳሽ ፡ በሶስተኛ፡ ወገን፡ ላይ፡ ቀጥታዊ ፡ ክስ፡ እንዲያመጣ ፡ መፍቀድ ፡ ነው ።[42]

እንደ ፡ ደንቡ፡ግን፡ አንድ ፡ አበዳሪ ፡ ቀጥታዊ ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ የሚችለው ፡ ከተበዳሪው ፡ በተበደሩ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ባሁኑ ፡ ሁኔታ ፡ ውስጥ ፡ ግን ፡ ክሱ ፡ የሚቀርበው ፡ በሶስተኛ ፡ ደረጃ ፡ ተበዳሪ ፡ ላይ ፡ ሳይሆን ፡ በደፈናው ፡ ተካፋይ ፡ በሆነ ፡ በሶስተኛ ፡ ወገን ፡ ላይ ፡ ነው ።

አልሞሰኒኖም ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስ ፡ በቀላሉ ፡ እንዲፈቀድ ፡ አያደርግም ።[43] ከሳሹ ፡ ሶስተኛውን ፡ ወገን ፡ መክሰስ ፡ የሚችለው ፡ የከሰረው ፡ ወገን ፡ አበዳሪ፡ እርሱ ፡ ብቻ ፡ ሲሆን ፡ ነው ። ሌሎች ፡ አበዳሪዎች ፡ ካሉ ፡ ግን ፡ ተተኪውን ፡ ክስ ፡ መፍቀድ ፡ ከሌሎቹ ፡ ይልቅ ፡ ቅድሚያ ፡ መስጠት ፡ ስለሚሆን ፡ አይገባም ፡ ይላል ። ስለዚህ ፡ እንደ ፡ ሌላው ፡ አበዳሪ ፡ ተቆጥሮ ፡ ከሶስተኛው ፡ ወገን ፡ ንብረት ፡ በመካፈል ፡ የሚያደርሰውን ፡ መቀበል ፡ አለበት ።

ፍርድ ፡ ቤቶቹም ፡ የያዙት ፡ አስተያየት ፡ አብዛኞቹ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ካሉት ፡ ጋር ፡ የሚስማማ ፡ ነው ። በ፩ሺ፱፻፵፱ ፡ የካሳስዮን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይህንኑ ፡ መስመር ፡ በመከተል ፡ የሚከተለውን ፡ አንድ ፡ የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ አጽንቶታል ።[44]

አንድ ፡ ሰው ፡ ከአንድ ፡ ኩባንያ ፡ ላይ ፡ ቤት ፡ ገዛና ፡ ለማደስ ፡ የሥራ ፡ ተቋራጭ፡ ቀጠረ ፤ በመሀሉ ፡ ስለከሰረ ፡ ኩባንያውንም ፡ የሥራ ፡ ተቋራጩንም ፡ ለመክፈል ፡ ሳይችል ፡ ቀረ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ኩባንያው ፡ ቤቱን ፡ መልሶ ፡ ወሰደ ። የሥራው ፡ ተቋራጭ ፡ የቤቱን ፡ ገዢ ፡ በውላቸው ፡ መሠረት ፡ ለመክሰስ ፡ ይችል ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ገዢ ፡ ስለከሰረ ፡ እርሱን ፡ መክሰሱ ፡ ምንም ፡ ጥቅም ፡ ስለማይሰጠው ፡ ባላግባብ ፡ መበልጸግ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ክስ ፡ በኩባንያው ፡ ላይ ፡ አቀረበ ፡ ይህንንም ፡ ያደረገበት ፡ ምክንያት ፡ የቤቱ ፡ ባለቤት ፡ በከሳሽ ፡ ሥራና ፡ ንብረት ፡ ስለበለጸገ ፡ ነው ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ክሱን ፡ ተቀብሎታል ። በይግባኝ ፡ ላይ ፡ የከሳስዮን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፍርዱን ፡ አጽንቶታል ።

፬/ ሃብቱ ፡ ያላግባብ ፡ የተቀነሰበት ፡ ወገን ፡ ሌላ ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ ሲችል ፡ ይህንትቶ ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስ ፡ ሊያቀርብ ፡ ይችላልን ?

የጸሐፊዎች ፡ አስተያየት ፡ የሚያዘነብለው ፡ አይችልም ፡ ወደሚለው ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ ማዞና ፡ ማዞ ፡ “ሃብቱ ፡ የተቀነሰበት ፡ ወገን ፡ በውል ፡ ከውል ፡ ውጪ ፡ ባለ ፡

41. ጐሬ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ቍ ፩፻፹ ፡ ገጽ ፡ ፩፻፹፬

42. ቍ. ፩ሺ፩፻፳፩ ፡ ውል ፡ ውጤት ፡ የሚኖረው ፡ በተዋዋዮች ፡ መሐል ፡ ነው ፡ ይላል ። በቍ፡ ፩ሺ፩፻፳፮ መሠረት ፡ ግን ፡ አበዳሪ ፡ የተበደረውን ፡ ተበዳሪ ፡ መክሰስ ፡ ይችላል ። ይህ ፡ የሚቻለው ፡ ግን ፡ የመጀመሪያው ፡ ተበዳሪ ፡ የራሱን ፡ ተበዳሪ ፡ ለመክሰስ ፡ መብት ፡ ሲኖረው ፡ ነው ።

43. አልሞሰኒኖ ፡ ላንሪቸስማ ፡ ሳን፡ኮዝ ፡ ኤ ፡ ሳን ፡ ካራክቴር ፡ ሱብሲዲየር ፡ (፩ሺ፱፻፴፩) ፡ ቍ. ፹፫ ፡ ገጽ ፩፻፳፮ እና ፡ ተከታይ ፤ በቻሊስ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ገጽ ፡ ፩፻፳፪-፩፻፳፫ ፡ ውስጥ ፡ እንደቀረበው ።

44. ከሳሽ ፡ ሶሲየቴ ፡ ዲዝቢታሲዮ ፡ ቦን ፡ ማርሼ ፡ ደ ፡ ሳን ፡ ስርቫን ፡ ተከሳሽ ፡ ጕርኸር ፡ ዲ ፡ ኤች ፡ ፲፱፻፵ ፡ ፩፻፺ ፤ በከፊል ፡ በማዞና ፡ ማዞ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ገጽ ፡ ፮፻፵፪ - ፮፻፵፫ ፡ ፬ሺ፮፻፵፰ - ፮፻፵፱ ውስጥ ፡ እንደተገለጠ ።

ግዴታ ፣ በማይገባ ፡ በመክፈል ፣ ባልተፈቀደ ፡ ውክልና ፣ ወይም ፡ ባንድ ፡ በግዙፍ ፡ መብት ፡ የተመሠረተ ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ የሚችል ፡ ከሆነ ፡ የደ ፡ ኤን ፡ ሬም ፡ ቬርሶ ፡ ክስ ፡ የተከታይነት ፡ ጠባይ ፡ የተጠቀሱትን ፣ የክስ ፡ መሠረቶች ፣ ትቶ ፡ ባላግባብ ፡ መበ ልጸግ ፣ መሠረት ፡ ክሱን ፡ ከማቅረብ ፡ ያግደዋል ።"[45]

በማርቲና ፡ ሬኖ ፡ አስተያየት ፡ "ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ሕጐች ፡ የተፈጠሩት ፡ በዳኝነት ፡ ሲሆን ፡ ላፈጣጠራቸውም ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ በሕጉ ፡ ውስጥ ፡ የሚገ ኘውን ፡ ጉድለት ፡ ለማሟላት ፡ ስለሆነ ፡ ከሳሽ ፡ ሊጠቀምባቸው ፡ የሚችለው ፡ ሕጉ ሌላ ፡ የክስ ፡ ዘዴ ፡ ሳይሰጠው ፡ ሲቀር ፡ ብቻ ፡ ነው ።"[46]

ጎሬም ፡ ለከሳሹ ፡ ምርጫ ፡ አይፈቅድም ፤ ይህንንም ፡ የሚለው ፡ በፈረንሣዊ ፡ የሕግ ፡ ምንጮች ፡ ደረጃ ፡ አመዳደብ ፡ መሠረት ፡ ነው ።[47] በዚህ ፡ የሕግ ፡ ሃሳብ ፡ መሠረት ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔዎችና ፡ ከልማድ ፡ የሚመነጩ ፡ ሕጐች ፣ የሚታሰ ቡት ፡ ከሕግ ፡ አውጪው ፡ ክፍል ፡ ከወጡት ፡ ሕጐች ፡ በታች ፡ ነው ። ያላግባብ ፡ መበ ልጸግ ፡ ክስም ፡ በፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የተፈጠረ ፡ ሃሳብ ፡ ስለሆነ ፡ ሕጉ ፡ ለከሳሹ ፡ ሌላ ፡ የክስ ፡ መንገድ ፡ ሲፈቅድለት ፡ ይኸኛው ፡ ቀርቶ ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስ ፡ ሊተ ካ ፡ አይችልም ።[48] በፕላንዮልና ፡ ሪፔር ፡[49] ፡ አስተያየት ፡ የክስ ፡ ዘዴ ፡ ማማረጥ ፡ ጉዳይ ፡ በውል ፡ ውስጥ ፡ ሊነሳ ፡ አይችልም ፣ ስልጣን ፡ ሳያገኝም ፡ በሚሠራ ፡ ወኪል፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ የመነሳቱ ፡ ዕድል ፡ በጣም ፡ የመነመነ ፡ ነው ። የመምረጡ ፡ ጉዳይ ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ በሚነሳ ፡ ክስ ፡ ውስጥ ፡ ሊኖር ፡ ይችላል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስ ፡ የማይሠራበት ፡ ምክንያት ፡ በመበልጸጉና ፡ ሀብት ፡ በማጣቱ ፡ መካ ከል ፡ የምክንያታዊ ፡ ግንኙነት ፡ እንዲኖር ፡ ስለሚያስፈልግ ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከሳሹ ፡ የፈለገውን ፡ የክስ ፡ ዓይነት ፡ ለመምረጥ ፡ ሙሉ ፡ መብት ፡ እንዲኖረው ፡ ያስፈልጋል ፡ ወደሚሉት ፡ ጸሐፊዎች ፡ እናምራ ። ቻሊስ ፡[50] እንደሚ ለው ፡ ይህን ፡ አስተያየት ፡ የሚያቀርቡት ፡ አዳዲስ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ናቸው ። እነዚህ ፡ ጸሐፊዎች ፡ የሚሉት ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ተከታይነት ፡ ጠባይ ፡ የሚሠራው ፡ ሕጉ የሚያዘውን ፡ ባልፈጸመ ፡ ከሳሽ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ለምሳሌ ፡ ቻሊስ ፡ እንደሚለው ፡ ኤስማይን፡ ለቁ ፡ ፩ሺ፰፻፲፩ ፡ ፩-ሺ ፩፻፳፩ ፡በሰ ጠው ፡ አስተያየታዊ ፡ ማብራሪያ ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስ ፡ ተከታይነት ፡ እንደሚ ከተለው ፡ መግለጽ ፡ አለበት ፡ ብሏል ።

የደ ፡ ኤን ፡ ሬም ፡ ቬርሶ ፡ ክስ ፡ መቅረብ ፡ የማይችለው ፡ ከሳሹ ፣ በይርጋ ፡ ምክን ያት ፡ ወይም ፡ የሚገባውን ፡ ማስረጃ ፡ ማቅረብ ፡ ባለመቻሉ ፡ ሌላ ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ ሳይችል ፡ ሲቀር ፡ ብቻ ፡ ነው ።

---

45. ማዞና ፡ ማዞ ፣ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ቍ ፡ ፲፱፺ ፡ ገጽ ፡ ፲፱፵፪ ፡
46. ማርቲና ፡ ሬይኖ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ቍ ፡ ፫፻፶፫ ፡ (፪) ገጽ ፡ ፫፻፳
47. ጐሬ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ቍ- ፩፻፶፱-፪፻፬- (ገጽ ፡ ፪፻፪-፪፻፱) ፡ ይህ ፡ የሕግ ፡ ደረጃ ፡ አመዳደብ ፡ በዚህ ፡ ክፍል ፡ ወደ ፡ መጨረሻው ፡ ላይ ፡ ይዘረዘራል ።
48. እላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ ቍ ፪፻፹፰ ፡ ገጽ ፡ ፫፻-፫፻፩
49. ፕላኒዮልና ፡ ሪፔር ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ቍ- ፯፻፷፫ ፡ (፩) ፡ ገጽ ፡ ፸፪ ፡
50. ቻሊስ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ገጽ ፡ ፩፻፳፭ ፡
51. ከዚያው ፡ ገጽ ፡ ፩፻፳፯

በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ በቤልጅግና ፡ በፈረንሣይ ፡ ሕግ ፡ መካከል ፡ ተመሳሳይነት ፡[52] ስላለ ፡ የቤልጅግ ፡ ጸሐፊዎች ፡ የሚሰጡትን ፡ አስተያየት ፡ መመልከት ፡ ይጠቅማል ። ሩት ሴርት ፡[53] ሁለት ፡ ክሶች ፡ ሊቀርቡ ፡ ሲችሉ ፡ ከሳሹ ፡ በአንደኛው ፡ ብቻ ፡ እንዲወሰን ፡ ማድረግ ፡ ምክንያቱ ፡ ግልጽ ፡ አይደለም ፡ ይላል ። አልሞሲኖና ፡[54] ቤጌም ፡ ተመሳሳይ ፡ አስተያየት ፡ አላቸው ፡ ይባላል ።

እንደ ፡ ምሁራት ፡ በአስተያየት ፡ ሳይለያዩ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ "አንድ ፡ ከሳሽ ፡ ሌላ ፡ የክስ ፡ መዋጮ ፡ ሲኖረው ፡ ባላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስ ፡ ሊተካው ፡ አይችልም ፡" ይላሉ ። ከክልየትና ፡ ብርያኖ ፡ ጉዳዮች ፡ ጀምረው ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስ ፡ ሁልጊዜ ፡ ቦታውን ፡ ለሌላው ፡ ክስ ፡ መልቀቅ ፡ እንዳለበት ፡ ወስነዋል ። ለምሳሌ ፡ በ፩ሺ፱፻፵፱ ፡ የካሳስዮን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንደሚከተለው ፡ ብሏል ።

"ባላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ የተመሠረተ ፡ ክስ ፡ ለመቅረብ ፡ የሚችለው ፡ በሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ መካከል ፡ ውል ፡ ሳይኖርና ፡ ሃብቱ ፡ የተቀነሰበት ፡ ወገን ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ በሚደርስ ፡ ግዴታ ፡ መክሰስ ፡ ሳይችል ፡ ሲቀር ፡ ብቻ ፡ ነው ።"[56]
በ፲፱፻፶፩ ፡ ደግሞ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንደሚከተለው ፡ የመጀመሪያ ፡ ሃሳቡን ፡ መልሶ ፡ አቅርቦታል ።

"የደ ፡ ኤን ፡ ሬም ፡ ቬርሶ ፡ ክስ ፡ በተፈጥሮው ፡ በሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ወይንም ፡ በተከታይነት ፡ ብቻ ፡ የሚቀርብ ፡ ክስ ፡ ስለሆነ ፡ ክሱ ፡ ሊቀርብ ፡ የሚችለው ፡ በውል ፡ ወይም ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ በሚፈጠር ፡ ግዴታ ፡ ሊመሠረት ፡ የማይችል ፡ ሲሆን ፡ ብቻ ነው ።"[57]

እላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ አነጋገር ፡ ጉዳዩን ፡ በደንብ ፡ አይገልጸውም ፡ ምክንያቱም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ባላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተውን ፡ ክስ ፡ ያልተቀበለው ፡ ሌላ ፡ ክስ ፡ ሊተካ ፡ ስለማይችል ፡ ሳይሆን ፡ ከሳሹ ፡ ሕጉ ፡ የሚያዘውን ፡ ባለመፈጸሙ ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ የክልየትና ፡ የብርያኖ ፡ ጉዳዮች ፡ ሁለቱም ፡ ተቀባይነት ፡ ያላገኙት ፡ ሕጉ ፡ የሚያዘውን ፡ ስለሚጻረሩ ፡ ነው ።

ኢንሳይክሎፒዲ ፡ ዳሎዝ ፡[58] ይህንኑ ፡ ሲያረጋግጥ ፡ እንደ ፡ ቻሊስ ፡[59] ያሉ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ደግሞ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ተመሳሳይ ፡ ውሳኔ ፡ ሌላ ፡ ምክንያት ፡ ነበር ፡ ይላሉ ። ለማንኛውም ፡ በፍርድ ፡ ቤቶች ፡ አስተያየት ፡ የደ ፡ ኢን ፡ ሬም ፡ ቬርሶ ፡ ክስ ፡ ለፍትሕ፡

52. ቻሊስ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ገጽ ፡ ፩፻፳ ፡
53. ሩትሴር ፡ "ዱ ፡ ካራክቴር ፡ ኖን ፡ ሱብሲዲዬር ፡ ደላክሲዮን ፡ ደላንሪሽስማ ፡ ሳን ፡ ኮዝ" ሬቩ ፡ ዱ ፡ ድሮዋ ፡ ቤልዥ ፡ ፩ሺ፱፻፴፯ ፡ ቀ— ፲፫ ፡ ገጽ ፡ ፴ ፡ በቻሊስ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ገጽ ፡ ፩፻፳፰ ፡ እንደቀረበው ።
54. አልሞሶኒኖ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ቀ— ፹፯ ፡ ገጽ ፡ ፩፻፹፯ ፡
55. ቤጌ ፡ "ላንሪሽስማ ፡ ሳን ፡ ኮዝ" ፓሪ ፡ ፩ሺ፱፻፵፰ ፡ ቀ— ፩፻፵፯ ፡ ገጽ ፡ ፪፻፲ ፡ ቀ— ፩፻፶፬ ፡ ገጽ ፡ ፪፻፳፰
56. ቡል ፡ ካሳሲዮ ፡ ሲቪል ፡ ፩ሺ፱፻፵፱ ፡ ፮፻፵፩ ፡ በድራኪዲስ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ገጽ ፡ ፮፻፩ እንደተጸፈ ።
57. ቡል ፡ ካሳስዮ ፡ ሲቪል ፡ ፩ሺ፱፻፶፩-፩-፳፯ ፡ በድራካዲስ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ገጽ ፡ ፮፻፩ እንደተጻፈ
58. ዳሎዝ ፡ ኤንሲክሎፒዲ ፡ ዡሪዲክ ፡ ደ ፡ ድሩዋ ፡ ሲቪል ፡ (፲፱፻፶፪) ቮልዩም ፡ ፪ ፡ አንሪሽዘማ ፡ ሳን ፡ ኮዝ ቀ— ፩፻፴፩
59. ቻሊስ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ገጽ ፡ ፩፻፴

ሲባል ፡ በዳኝነት ፡ የተፈጠረ ፡ ስለሆነ ፡ ከሌላ ፡ ምንጭ ፡ ከመነጩ ፡ የክስ ፡ መነሻ ዎች ፡ ጋር ፡ ሊመጣጠን ፡ አይችልም ፡ ባዮች ፡ ናቸው ።

፫/ ከላይ ፡ ለተጠቀሱት ፡ አራት ፡ ሁኔታዎች ፡ አምስተኛ ፡ መጨመር ፡ ይቻላል። ጉዳዩ ፡ ግልጽ ፡ በመሆኑ ፡ አብዛኛዎቹ ፡ ጸሐፊዎች ፡ በጽሑፋቸው ፡ ውስጥ ፡ አይጨ ምሩትም ።[60] ይህ ፡ የሚሆነው ፡ ሃብቱ ፡ የተቀነሰበት ፡ ወገን ፡ በውል ፡ ወይም ፡ ከውል ውጭ ፡ ግዴታ ፡ የተመሠረተ ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ በማይችልበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ። ሕጉ ፡ ለሁኔታው ፡ የሚሰጠው ፡ የክስ ፡ መሠረት ፡ የለም ፡ ስለዚህ ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስን ፡ ማቅረብ ፡ ሕጉን ፡ በምንም ፡ ዓይነት ፡ አይጻረርም ፡ እንዲያውም ፡ በሕጉ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ያለመሟላት ፡ ለማሻሻል ፡ ሲባል ፡ የተፈጠረ ፡ ክስ ፡ ሆኖ ፡ ይገ ኛል ። በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ ክሱን ፡ የማይፈቅድ ፡ አይገኝም ።

የሚከተሉት ፡ ሁለት ፡ ጉዳዮች ፡ ሌላ ፡ ሊቀርብ ፡ የሚችል ፡ ክስ ፡ ሳይኖር፡ ያላግባብ፡ መበልጸግን ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ ይቻላል ፡ የሚለው ፡ አነጋገር ፡[61] ምን ፡ ማለት ፡ እንደ ሆነ ፡ ያስረዳሉ ።

በመጀመሪያው ፡ ጉዳይ ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ በፈረንሣይ ፡ ሃገር ፡ ውስጥ ፡ ኑዛዜ ፡ ሳታ ደርግ ፡ ካረፈች ፡ በኋላ ፡ ንብረቷ ፡ ይገባቸዋል ፡ ለተባሉ ፡ ወራሾች ፡ ተሰጠ ። አንድ ፡ ሥራው ፡ የሰውን ፡ ትውልድ ፡ ማጥናት ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ መውረስ ፡ የሚገባቸው ፡ የሟቿ የወንድም ፡ ልጆች ፡ መኖራቸውን ፡ በምርምር ፡ ደረሰበት ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እነርሱን ፡ አግኝቶ ፡ ውርስ ፡ እንዳላቸው ፡ ከነገራቸው ፡ በኋላ ፡ መጠኑንና ፡ የሚገኝበትን ፡ ዘዴ ፡ እንዲነግራቸው ፡ ከፈለጉ ፡ ከውርሱ ፡ ሊያካፍሉት ፡ ውል ፡ እንዲገቡ ፡ ጠየቃቸው ። ውርስ ፡ እንዳላቸው ፡ ካወቁ ፡ በኋላ ፡ በፈረንሣይ ፡ የሚገኘውን ፡ የአሜሪካን ፡ ቆንሲል፡ አግኝተው ፡ ጉዳዩን ፡ እንዲያጣራላቸው ፡ ከጠየቁ ፡ በኋላ ፡ ዕውነት ፡ ሆኖ ፡ ስላገ ኙት ፡ መዋዋል ፡ አለመፈለጋቸውን ፡ ለሰውየው ፡ ነግረው ፡ የሚገባቸውን ፡ ድርሻ ፡ አገኙ ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ የሰው ፡ ዘር ፡ የሚያጠናው ፡ ሰው ፡ ለሰጣቸው ፡ መረጃ ፡ ገን ዘብ ፡ እንዲከፍሉት ፡ ክስ ፡ አቀረበ ፡ ተከሳሾቹም ፡ የከሳሽ ፡ ጉዳይ ፡ ውድቅ ፡ እንዲሆንላቸው ፡ ጥያቄ ፡ አቀረቡ ፤ የሰጡትም ፡ ምክንያት ፡ ክሱ ፡ በውል ፡ ወይንም በእንደራሴነት ፡ መጠን ፡ ያልተፈጸመ ፡ በመሆኑ ፡ መነሾ ፡ ሊኖረው ፡ የማይችል ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ነበር ። ክሱ ፡ የቀረበለት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነገሩን ፡ አይቶ ፡ በሌላ ፡ ሰው፡ ምክንያት ፡ የሚበለጽግ ፡ ሰው ፡ የሚገባውን ፡ ክፍያ ፡ ካላደረገ ፡ በደ ፡ ኢን ፡ ሬም ፡ ቬርሶ ፡ መክሰስ ፡ ይችላል ፡ ብሎ ፡ ክሱን ፡ ተቀበለው ፤ በይግባኝ ፡ የካሳሲዮን ፡ ፍርድ፡ ቤትም ፡ ፍርዱን ፡ አጸናው ።

ሁለተኛው ፡ ጉዳይ ፡ ደግሞ ፡ እንደሚከተለው ፡ ነበር ።[62] ከሳሽ ፡ በተከሳሽ ፡ ቤት ፡ በግርድና ፡ ተቀጥራ ፡ ስትሠራ ፡ ከቆየች ፡ በኋላ ፡ ተከሳሽ ፡ ሚስቱን ፡ ፈታ ፤ ከዚ ያም ፡ ከሳሽን ፡ በውሽምነት ፡ ያዛት ። እንደሚያገባት ፡ ከገለጸላትም ፡ በኋላ ፡ ከርሱ ፡ ደመወዝ ፡ መቀበሏን ፡ ትታ ፡ አብረው ፡ ኑሯቸውን ፡ ቀጠሉ ። ሰባት ፡ ዓመት ፡ በዚህ፡ ዓይነት ፡ መተሳሰር ፡ ከቆዩ ፡ በኋላ ፡ ሊያገባት ፡ እንደማይፈቅድ ፡ ነገራትና ፡ ሁኔታው፡ ወደ ፡ ፍጻሜ ፡ ደረሰ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከሳሽ ፡ ሰላሳ ፡ አምስት ፡ ሺህ ፡ ፍራንክ ፡ በመጠ የቅ ፡ ከሰሰችው ። ለክሷ ፡ መሠረት ፡ አድርጋ ፡ ያቀረበችው ፡ ሁለት ፡ ነገር ፡ ነበር ።

---

60. ድራኪዲስ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ገጽ ፡ ፩፻፺፰ ከሚገኙት ፡ ጥቂቶቹ ፡ አንዱ ፡ ነው ።

61. ከሳሽ ፡ ኮንሰር ፡ ዱቡርግ ፡ ተከሳሽ ፡ አንትዋን ፡ ዲ ፡ ፩ሺ፱፻፷፫ ፱ ፫፻፴፱

62. ከሳሽ ፡ ለብላን ፡ ተከሳሽ ፡ ደምቪያል ፡ ዲ ፲፱፻፳፫ ፱ ፩፻፷፱ ፡

የመጀመሪያው ፡ ሊያገባት ፡ ቃል ፡ ከገባ ፡ በኋላ ፡ ቃሉን ፡ ባለመጠበቁ ፡ ሁለተኛው ፡ ደግሞ ፡ ለሰባት ፡ ዓመት ፡ ገንዘብ ፡ ሳትከፈል ፡ ስላገለገለችው ፡ ነው ። የመጀመሪያው የክስ ፡ መሠረት ፡ የኛን ፡ ዓላማ ፡ የማይመለከት ፡ ስለሆነ ፡ ሁለተኛውን ፡ ብቻ ፡ እን መለከታለን ።[63] በሁለተኛው ፡ የክስ ፡ መሠረት ፡ የተመለከተውን ፡ ክስ ፡ የካሳስዮን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተመልክቶ ፡ የተፈጸመ ፡ ውል ፡ ስለሌለ ፡ ከሳሽ ፡ በደ ፡ ኢን ፡ ሬም ፡ ቬርሶ ፡ ገንዘቧን ፡ መከፈል ፡ ይገባታል ፡ ሲል ፡ ፈረደ ። የሰጠውም ፡ ምክንያት ፡ ተከ ሳሿ ፡ በከሳሽ ፡ ጉልበት ፡ በመጠቀምና ፡ ገንዘብ ፡ ባለመክፈሉ ፡ ለገረዶች ፡ መከፈል ፡ የሚኖርበትን ፡ ገንዘብ ፡ ስላዳነ ፡ ያለ ፡ ምክንያት ፡ በልጽጓል ፡ የሚል ፡ ነበር ።

፫/ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ በሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ብቻ ፡ ተጠቃሽ ፡ የሚሆንበት ፡ ጊዜ ።

ከላይ ፡ በቀረቡት ፡ የጸሐፊዎች ፡ አስተያየቶችና ፡ የፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ውሳኔዎች ፡ አላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ክስ ፡ በተከታይነት ፡ ወይም ፡ በሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ብቻ ፡ ሊቀርብ ፡ የሚችል ፡ ክስ ፡ ነው ፡ ለሚለው ፡ መሠረተ ፡ ሃሳብ ፡ መግለጫ ሆነው ፡ የሚቀርቡ ፡ ሁለት ፡ ንጥረ ፡ አሳቦች ፡ እንዳሉ ፡ እንረዳለን ።

አንደኛው ፡ ምክንያት ፡ በሕጐች ፡ የበላይና ፡ የበታች ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ነው ። የዚህ ፡ ሃሳብ ፡ ደጋፊዎች ፡ በፈረንሣይ ፡ የሕግ ፡ ቅንጅት ፡ መሠረት ፡ በሕግ ፡ አውጪው ፡ ክፍል ፡ የወጡት ፡ ሕጐች ፡ የበላይነት ፡ ደረጃ ፡ ሲሰጣቸው ፡ ሌሎች ፡ ሕጐች ፡ የበታች ፡ ናቸው ።[64] ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ በልማድ ፡ የተፈጠረና ፡ ክሱ ፡ የመነጨው ፡ ክስ ፡ በፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የሚጨበጥ ፡ ትርጉም ፡ የተሰጠው ፡ ስለሆነ ፡ ደረጃው ፡ የበታችነት ፡ ነው ፡ ይላሉ ። ሕጉ ፡ አንድ ፡ መፍትሔ ፡ በሚያበረክትበት ፡ ጊዜ ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስ ፡ ሊቀርብ ፡ አይችልም ።

በሩዋስት ፡ አስተያየት ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ምንጭ ፡ የተፈጥሮ ፡ ሕግ ፡ ነው ። አንድ ፡ ሰው ፡ በሌላው ፡ ሰው ፡ ምክንያት ፡ አላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ የለበትም ፡ ከሚል ፡ ፍትሐዊ ፡ አስተያየት ፡ የመነጨ ፡ ነው ። ይህን ፡ ሃሳብ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የመብትና ፡ ግዴታ ፡ ምንጭ ፡ አድርገው ፡ የተወሰነ ፡ መልክ ፡ ሰጥተውታል ። ጎሬም ፡[65] ተመሳ ሳይ ፡ አስተያየት ፡ አለው ። ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ሕግ ፡ ከልማድ ፡ የመነጨ ፡ ነው ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ ለልማድ ፡ ሕግ ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ ትርጉም ፡ ይሰጠዋል ። በርሱ ፡ አስተያየት የልማድ ፡ ሕግ ፡ "ሕግ ፡ አውጪ ፡ ክፍል ፡ ካወጣው ፡ ሕግ ፡ በስተቀር ፡ ሌላውን ፡ ሁሉ ፡ የሚጨምር ፡ ነው ።" ከሩዋስት ፡ ጋር ፡ የማይስማማው ፡ ይህ ፡ የልማድ ፡ ሕግ ስለመጣበት ፡ መንገድ ፡ ነው ። በሩዋስት ፡ አስተያየት ፡ "ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ሕግ፡ የተፈጠረው ፡ በፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሳይሆን ፡ በልማድ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ግን ፡ ልማዱን ፡ ሕግ ፡ እንዲሆን ፡ አድርገውታል ።"[67] በጎሬ ፡ አስተያየት ፡ ግን ፡

63. ስለ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ አልጨመርንም ፡

64. ሩዋስ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ቍ ፴፰ና ፡ የሚከተለው ፡ ድራኪዲስ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አር ዕስት ፡ ቍ ፴፫ ፡ ገጽ ፡ ፲፻፬-፲፻፭ ፡ ውስጥ ፡ እንደተጠቀሰ ፤ ጐሬ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ቍ ፩፻፬ ፡ ገጽ ፡ ፩፻፯-፩፻፱ ፤ ፕላኒዮልና ፡ ሪፔር ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ቍ ፲፻፷፩ ፡ ገጽ ፡ ፷፯ ፡

65. ላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ ቍ—፩፻፩ ፡ ገጽ ፡ ፩፻፲ ፺፰ ፡ ቀጥሎ ።

66. እዚያው ፡

67. ሩዋስ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ቍ. ፴፰ ፡ ገጽ ፡ ፩፻፬ ፡ ማስታወሻ ፡ ቍ. ፩ ፡ በቍ. ፩፻፪ ፡ ገጽ ፡ ፩፻፰ ፡ እንደቀረበው ።

ልማዱ ፡ በፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ዋጋ ፡ እንዲሰጠው ፡ ባይደረግ ፡ ኖሮ ፡ ልማድ ፡ ሆኖ ፡ ይቀር፡ ስለነበረ ፡ የሕጉ ፡ ምንጭ ፡ መሆን ፡ ያለባቸው ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ናቸው ፡ የሚል ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ የራሱንና ፡ የሩዋስትን ፡ ክርክር ፡ በመያዝ ፡ ቦንካስ ፡[68] ያቀረበውን ፡ ትችት ፡ ተቋቁሟል ። ቦንካስ ፡ የሚለው ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስ ፡ ሁለተኛ ፡ ተጠቃሽነት ፡ በልማድ ፡ ሕግና ፡ በተጻፈው ፡ ሕግ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ በመመልከት ፡ የተፈጠረ ፡ ሁኔታ ፡ አይደለም ፡ነው ። ጎሬ ፡ ግን ፡ ለሩዋስት ፡ ሲከራከር ፡ ሩዋስት ፡ የልማድ ፡ ሕግ ፡ ከተጻፈ ፡ ሕግ ፡ በታች ፡ ነው ፡ አላለም ፡ ሲል ፡ ተከራክሯል ። ሩዋስት ፡ ያመለከተው ፡ ሕግ ፡ አውጪው ፡ ክፍል ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ ዘዴ ፡ አንድ ፡ ሕግ ፡ ባወጣበት ፡ ጊዜ ፡ ስለዚሁ ፡ ሁኔታ ፡ የልማድ ፡ ሕግ ፡ ቢኖርም ፡ ደረጃው፡ ከተጻፈው ፡ ሕግ ፡ ጋራ ፡ ሊመጣጠን ፡ እንደማይችል ፡ ነው ። የልማድ ፡ ሕግ ፡ የሚያገለግለው ፡ በደንበኛው ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ ጉድለቶች ፡ ለማሟላት ፡ ብቻ ፡ ነው ።[69]

ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ጎሬ ፡ ስለ ፡ ልማድ ፡ ሕግ ፡ ደረጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ያላቸውን ፡ ግምት ፡ ያቀርባል ። አንዳንድ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ሕግ ፡ አውጪው ፡ ያወጣቸው ፡ ሕጐች ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሳይውሉ ፡ በሚቀሩበት ፡ ጊዜ ፡ የልማድ ፡ ሕግ ፡ እንዲተካቸው ፡ ያስፈልጋል ፡ የሚሉ ፡ አሉ ። ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ሕግ ፡ ባወጣው ፡ ክፍል ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ ሁኔታ ፡ እንዲለወጥ ፡ ካልተደረገ ፡ በስተቀር ፡ ሕግ ፡ ሆኖ ፡ ይቆያል ፡ ይላሉ ። "ስለዚህ ፡ በፍርድ ፡ ቤቶች ፡ አስተያየት ፡ የልማድ ፡ ሕግ ፡ በሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ያለ ፡ የሕግ ፡ ምንጭ ፡ ነው ። ያላግባብ ፡ መበልጸግም ፡ መስየ ፡ ሩዋስት ፡ እንዳሉት ፡ የልማድ ፡ ሕግ ፡ ስለሆነ ፡ በሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ብቻ ፡ ሊቀርብ ፡ የሚችል ፡ ክስ ፡ መሆን ፡ አለበት ።"[70]

በመጨረሻ ፡ ጎሬ ፡ ይህ ፡ ሃሳብ ፡ "ሕጉ ፡ ላይ ፡ ሽፍጥ ፡ ስለመስራት" ጉዳይ ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ እንደሌለውና ፡ ትርጉሙ ፡ ደንበኛው ፡ ሕግ ፡ መፍትሔ ፡ ሲያበረክት ፡ ተተክቶ ፡ መቅረብ ፡ የማይችል ፡ መሆኑን ፡ ብቻ ፡ የሚያሳይ ፡ ነው ፡ ይላል ።[71]

ቦንካስ ፡[72] ሌላ ፡ መንገድ ፡ በመያዝ ፡ ከላይኛው ፡ ጋር ፡ የሚመሳሰል ፡ መደምደሚያ ፡ ላይ ፡ ይደርሳል ። ጉዳዩን ፡ በሥልጣን ፡ ማከፋፈል ፡ ረገድ ፡ ይመለከተዋል ። ዳኞች ፡ በሚያስችሉበት ፡ ጊዜ ፡ ሕግ ፡ አውጭው ፡ ክፍል ፡ ባወጣው ፡ ሕግ ፡ መገልገል ፡ አለባቸው ። ልማድንና ፡ ፍትሐዊ ፡ አስተያየታቸውን ፡ መመልከት ፡ ያለባቸው ፡ ሕጎቹ ፡ ያልተሟሉ ፡ ሲሆኑ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ልማድ ፡ ወይም ፡ ፍትሐዊ ፡ አስተያየት ፡ የሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ተጠቃሚነት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ያለው ። በዚሁ ፡ መሠረት ፡ በልማድ ፡ ወይም ፡ በፍትሐዊ ፡ አስተያየት ፡ ላይ ፡ የተመሠረቱ ፡ ክሶች ፡ ተጠቃሽነታቸው ፡ በሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ መሆን ፡ አለበት ፡ ምክንያቱም ፡ ምንጮቻቸው ፡ በሕግ ፡ ቅደም ፡ ተከተል ፡ ሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ስለሆኑ ፡ ነው ።

---

68. ቦንካዝ ፡ ሱፕለማን ፡ አ ፡ ትሬቴ ፡ ቲኦሪክ ፡ ኤ ፡ ፕራቲክ ፡ ደ ፡ ድርዋ ፡ ሲቪል ፡ ደ ፡ ቦድርይ - ላካንቲነሪ (፲፰፻፺፯) ቮልዩም ፡ ፫ ፡ ገጽ ፡ ፪፻፺፯ ፡ በጐሬ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ውስጥ ፡ ቊ ፡ ፪፻፩ ገጽ ፡ ፪፻፬ ፡ እንደቀረበ ።
69. ጐሬ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ቊ ፡ ፪፻፫ ፡ ገጽ ፡ ፪፻፮ ፡
70. እዚያው ፡ ቊ ፡ ፪፻፬ ፡ ገጽ ፡ ፪፻፯-፪፻፰ ፡
71. እዚያው ፡ ገጽ ፡ ፪፻፱ ፡
72. ቦንካዝ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ በጐሬ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ገጽ ፡ ፪፻፱ ፡ በአተራረክ ፡ መልክ ፡ እንደቀረበው ፡

ሌላው ፡ ስለ ፡ ተከታይነት ፡ ጠባይ ፡ አጠቃላይ ፡ ሃሳብ ፡ ደግሞ ፡ "ፍሮድ ፡ አ ፡ ላ ፡ ሉዋ ፡ " የተባለውን ፡ ለማስወገድ ፡ የሚጥረው ፡ ነው ። የዚህ ፡ ሃሳብ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ። ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስ ፡ በሕግ ፡ በተከለከለ ፡ ሌላ፡ ክስ ፡ ተተኪነት ፡ ሊቀርብ ፡ አይችልም ። የዚህ ፡ ምክንያት ፡ ደግሞ ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስ ፡ በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ እንዲፈቀድ ፡ ማድረግ ፡ ሕጉ ፡ ከሚያዘው ፡ መሸሽና ፡ የሕጉን ፡ ዓላማ ፡ ማፍረስ ፡ ስለሚሆን ፡ ነው ። የዚህ ፡ ሁኔታ ፡ ሁለት ፡ ምሳሌዎች ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ ክስ ፡ ተገቢውን ፡ የውል ፡ አጻጻፍ ፡ መልክ ፡ ካለመያዙ ፡ ውድቅ ፡[73] ሲሆንና ፡ ክሱ ፡ በይርጋ ፡ ምክንያት ፡ ሲታገድ ፡ የሚፈጠሩ ፡ ናቸው ። ድራኪደስ ፡ እንዳለው ፡ "ሕግ ፡ አውጪው ፡ ከሳሽ ፡ ተገቢውን ፡ ባለመፈጸሙ ፡ ለመክሰስ ፡ እንዳይችል ፡ ስላደረገው ፡ መክሰስ ፡ የሚያስችለውን ፡ መንገድ ፡ በተጠማዘዘ ፡ መንገድ ፡ መፍጠር ፡ ተገቢ ፡ አይደለም"። ፕላንዮልና ፡ ሪፔርም ፡[74] ጉዳዩን ፡ ሲያብራሩ ፡ "ሕግ ፡ ይርጋ ፡ የተባለውን ፡ ትእዛዝ ፡ ስለፈጠረ ፡ ይህንኑ ፡ በሚጻረር ፡ አኳኋን ፡ ሌላ ፡ ክስ ፡ እንዲኖረው ፡ ማድረግ ፡ አስቀድሞ ፡ ይርጋን ፡ እንዳለመፍጠር ፡ ነው" ፡ ብለዋል ። ስለ ዚህ ፡ ጸሐፊዎቹ ፡ ሃሳባቸውን ፡ በመቀጠል ፡ "ያስተሳሰብ ፡ ስርዓትና ፡ በተፈጥሮ ፡ የሚያጋጥሙት ፡ ሁኔታዎች ፡"[75] ጸሐፊዎችንና ፡ ፍርዶችን ፡ ያሁኑን ፡ መስመር ፡ እንዲከተሉ ፡ አድርጎአቸዋል ።

፬/ <u>"በቂ ፡ ምክንያት ፡" በተባለውና ፡ "ተከታይነት" ፡ በተባለው ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ መደራረብ ።</u>

ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስን ፡ የሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ተጠቃሽነት ፡ ወይም ፡ ተከታይነት ጠባይ ፡ ከመመርመራችን ፡ በፊት ፡ "በቂ፡ ምክንያት" ፡ የተባለውን ፡ ተመልክተናል ። አሁን ፡ ሁለቱን ፡ ስለተመለከትን ፡ በመካከላቸው ፡ ያለው ፡ ግንኙነት ፡ በምን ፡ ሁኔታና ፡ ዘዴ ፡ እንደሚፈጠር ፡ እንመለከታለን ።

ማዞና ፡ ማዞ ፡ በሁለቱ ፡ ሃሳቦች ፡ መካከል ፡ ብዙ ፡ መገናኘት ፡ መኖሩን ፡ እንደ ፡ ግልጽ ፡ ነገር ፡ አድርገው ፡ ይቀበሉታል ። "መበልጸጉ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ በሚኖረው ፡ ጊዜ ፡ የተከታይነት ፡ ሃሳብ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ከመጥፋት ፡ ጋር ፡ የተሳሰረ ፡ ነው ።"[76]

እላይ ፡ የጠቀስናቸውን ፡ "ለተከታይነት" ምክንያት ፡ የሆኑትን ፡ ሃሳቦች ፡ ስንመለከት ፡ ማዞና ፡ ማዞ ፡ ካሉት ፡ ጋር ፡ የሚስማማው ፡ ሐሳብ ፡ የትኛው ፡ ነው ? "የሕጎች፡ ቅደም ፡ ተከተል" ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ። ምክንያቱም ፡ ሀ) ፡ ይህ ፡ ሃሳብ ፡ የሚሠራው ፡ ብልጽግናው ፡ አለ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ሲፈጠር ፡ ነው ፤ እንዲሁም ፡ ለ) በዚህ ፡ ሃሳብ ፡ ምክንያት ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስ ፡ የሚከለከለው ፡ በውል ፡ ወይም ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ በሚፈጠረው ፡ ግዴታ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ሲሆን ፡ ነው ። አሁን ፡ ግን ፡ የምንነጋገረው ፡ ብልጽግናው ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ሲኖረውና ፡ ክሱ ፡ የሚከለከልበት ፡ ምክንያት ፡ አለ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ብልጽግናው ፡ የተፈጠረ ፡ መሆን ፡ አለበት ፡ የሚል ፡ ሕግ ፡ ስላለ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ "በቂ ፡ ምክንያት" ከሚለው ፡ ጋር ፡ የሚስማማው ፡ "ፍሮድ ፡ አ ፡ ላ ፡ ሉዋ ፡" የተባለው ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ በተተኪነት ፡ እንዳይቀርብ ፡ የሚያደርገው ፡ ሃሳብ ፡ መሆን ፡ አለበት ። ይህ ፡ መደምደሚያ ፡ ማዞና ፡ ማዞ ፡ ከሚሰጡት ፡ ምሳሌ ፡ ጋር ፡ የሚስማማ ፡ ነው ።

---

73. ድራኪዲስ ፡ <u>ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት</u> ፡ ቍ ፰ ፡ ገጽ ፩፻፺፩

74. ፕላኒዮልና ፡ ሪፔር ፡ <u>ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት</u> ፡ ቍ ፲፱፻፷፩ ፡ ገጽ ፡ ፰፰

75. እዚያው

76. ማዞና ፡ ማዞ ፡ <u>ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት</u> ፡ ቍ ፲፱፻፲፩ ፡ ገጽ ፡ ፲፱፻፶፩ ፡

ተጨማሪ ፡ መረጃ ፡ ለማግኘት ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ ጸሐፊ ፡ የሚሰጠውን ፡ አስተያየት ፡ እንመልከት ።

ሼቫልየ ፡ ተከታይነት ፡ የተባለው ፡ ሃሳብ ፡ ትርጉም ፡ እንደሌላው ፡ የደ ፡ ኢን ፡ ሬም ፡ ቬርሶ ፡ ክስ ፡ መጠን ፡ መታወቅ ፡ የሚችለው ፡ "በቂ ፡ ምክንያት ፡ " የተባለውን ፡ በመመርመር ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ይላል ። ሐተታውን ፡ እንደሚከተለው ፡ ጽፏል ፦

> ጸሐፊዎች ፡ ባላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተውን ፡ ክስ ፡ ውድቅ ፡ ማድረግ ፡ ስለሚገባበት ፡ ምክንያት ፡ ሲያብራሩ ፡ በተከታይነት ፡ ወይም ፡ በሁለተኛ ፡ ተጠቃሽነት ፡ ብቻ ፡ የሚቀርብ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ፡ ይላሉ ። ክሱ ፡ የማይፈቀድበት ፡ ምክንያት ፡ መበልጸጉ ፡ በሕግ ፡ ወይም ፡ በውል ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ስለሚገኝለት ፡ ነው ። "በቂ ፡ ምክንያት" ፡ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ትርጉም ፡ ሲሰጠው ፡ የተበለጸገበትን ፡ ንብረት ፡ ለማስመለስ ፡ በሚቀርብ ፡ ክስና ፡ ባለን ፡ የፍርድ ፡ ቅንጅት ፡ ጋር ፡ ስምምነት ፡ ሊፈጠር ፡ ይችላል ፤ ንብረቱን ፡ ለማስመለስ ፡ በሚቀርበው ፡ ክስ ፡ ምክንያት ፡ ሕጉ ፡ እንዳይ ፈርስ ፡ ያደርጋል ።[77]

በርሱ ፡ አስተያየት ፡ ለብልጽግናው ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ የሚሆኑት ፡ ውሎችና ፡[78] "ተከሳሹ ፡ በተከሰሰበት ፡ ክስ ፡ መክፈል ፡ እንዳይገደድ ፡ የሚያደርጉት ፡ ሕጎች ፡ ናቸው ። ሕጉ ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስን ፡ ውድቅ ፡ ሲያደርገው ፡ ለብልጽግናው ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ የለም ፡ ሊባል ፡ አይቻልም ። "[79] ክሱን ፡ ውድቅ ፡ የሚያደርጉ ፡ ሕጎች ፡ ለመኖራቸው ፡ ምሳሌ ፡ የሚሆኑ ፡ ብዙ ፡ ፍርዶች ፡ በምሳሌ ፡ ያቀርባል ። ስለ ዚህ ፡ በደፈናው ፡ "የተከታይነት" ጠባይ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ይህ ፡ ጠባይ ፡ "በቂ ፡ ምክንያት" ፡ ከሚባለው ፡ ጋር ፡ እንደተቀላለፈ ፡ ያስረዳል ። ስለዚህ ፡ የእርሱ ፡ ነቀፋ ፡ የተመሠረተው ፡ ክሱ ፡ የማይቀርብበት ፡ ምክንያት ፡ በሕጎች ፡ ቅደም ፡ ተከተልነት ፡ ነው ፡ በሚለው ፡ አስተያየት ፡ ላይ ፡ ነው ። ይህም ፡ በሩዋስት ፡ አስተያየት ፡ ላይ ፡ ከተሰጠው ፡ ትችት ፡ ጋር ፡ የሚስማማ ፡ አቋም ፡ ነው ።

"ፍሮድ ፡ አ ፡ ላ ፡ ሉዋ" ፡ ተብሎ ፡ የታወቀውና ፡ "በቂ ፡ ምክንያት" ፡ የሚባለው ፡ ሃሳብ ፡ የተያያዘ ፡ ነው ፡ ቢባል ፡ ተገቢ ፡ ይመስላል ። የመጀመሪያው ፡ ሃሳብ ፡ ሕጉ ፡ ባላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ የተመሠረተውን ፡ ክስ ፡ ሲያግድ ፡ ሁለተ ኛው ፡ ደግሞ ፡ ለመበልጸጉ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ሲኖር ፡ ክሱ ፡ ውድቅ ፡ ይሆናል ፡ የሚል ፡ ነው ። በመጀመሪያው ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ ሕግ ፡ በሌላ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ሊቆም፡ የሚችለውን ፡ ክስ ፡ በማገዱ ፡ "በቂ ፡ ምክንያት " ሲፈጥር ፡ በሁለተኛው ፡ መሠረት ፡ ግን ፡ ለብልጽግና ፡ ምንጭ ፡ የሆነው ፡ እንደ ፡ ውል ፡ ያለው ፡ ክንውን ፡ ነው "በቂ ምክንያት" ሆኖ ፡ ክሱን ፡ ውድቅ ፡ የሚያደርገው ። ስለዚህ ፡ በአሰራር ፡ ረገድ ፡ ሕጉ ፡ ዘግየት ፡ ብሎ ፡ ውጤቱን ፡ የሚያሳይ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ሕጉ ፡ ክሱን ፡ ውድቅ ፡ በማድ ረጉ ፡ "በቂ ፡ ምክንያት ፡" የተባለውን ፡ የሚፈጥር ፡ ነው ። በዚሁ ፡ መጠን ፡ እንግ ዲህ ፡ "ተከታይነት" ፡ በተባለውና ፡ "በቂ ፡ ምክንያት" በተባለው ፡ መካከል ፡ ጉልህ ፡ የሆነ ፡ መተሳሰር ፡ አለ ።

77. ሼባልዬ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ገጽ ፡ ፩፻፺፯ ፡
78. ላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ ገጽ ፡ ፩፻፺፫ —፩፻፺፬
79. ላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ ገጽ ፡ ፩፻፺፬
80. ላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ ገጽ ፡ ፩፻፺፯

## ፩/ መደምደሚያ ።

በፈረንሣይ ፡ ሕግ ፡ "ተከታይነት" የተባለው ፡ መሠረት ፡ አሳብ ፡ የሚከተሉትን፡ የሚያጠቃልል ፡ ነው ።

ሀ/ በውል ፡ ወይም ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ በሚፈጠር ፡ ግዴታ ፡ ላይ ፡ መመስረት ፡ የሚችል ፡ ክስ ፡ በሕግ ፡ ሲታገድ ፡ ወይም ፡ በከሳሹ ፡ ጥፋት ፡ ምክንያት ፡ ውድቅ ፡ ሲሆን ፡ ባላግባብ ፡ በመበልጸግ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ክስ ፡ ተተክቶ ፡ ሊያገለግል ፡ አይችልም ። በዚህ ፡ ሃሳብ ፡ ጸሐፊዎችና ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ባንድ ፡ ድምጽ ፡ የሚስማሙ ፡ ናቸው ።

በከሳሽ ፡ ጥፋት ፡ የተፈጠሩ ፡ ፍሬ ፡ ነገራዊ ፡ ጉድለቶችና ፡ በሕግ ፡ እክል ፡ ምክ ንያት ፡ የተፈጠሩ ፡ እንቅፋቶች ፡ የሚለዩት ፡ የመጀመሪያዎቹ ፡ በከሳሹ ፡ አለማወቅ ፡ ወይም ፡ ቸልተኛነት ፡ የሚፈጠሩ ፡ ሲሆኑ ፡ የሁለተኛው ፡ ግን ፡ ከከሳሹ ፡ ጋር ፡ ያልተ ያያዘ ፡ በሕጉ ፡ አሰራር ፡ ምክንያት ፡ የሚፈጠር ፡ ነው ። ልዩነቱ ፡ ይኸን ፡ ያህል ፡ የተብራራ ፡ አይደለም ፡ ስለዚህ ፡ ብዙ ፡ ጸሐፊዎች ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ይመለከቱታል ። ክሱ ፡ መከልከል ፡ አለበት ፡ ለሚለው ፡ ክርክር ፡ የሚቀርቡት ፡ ምክንያቶች ፡ ግን ፡ ይለያያሉ ። ፍርድ ፡ ቤቶችና ፡ አብዛኞቹ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ሕጉን ፡ የሚጻረር ፡ ሽፍጥ ፡ የሚፈጸምበት ፡ ስለሆነ ፡ አይቀበሉትም ፡ ሌሎች ፡ ደግሞ ፡ ክሱ ፡ ተቀባይነት ፡ የሚ ያጣበት ፡ ምክንያት ፡ ብልጽግና ፡ በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ ውስጥ ፡ ሲገኝ ፡ "በቂ ፡ ምክንያት" ስለሚኖረው ፡ ነው ፡ ይላሉ ።

ለ/ ፡ ተከሳሹ ፡ በውል ፡ ወይም ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ በሚነሳ ፡ ግዴታ ፡ መሠረት ፡ ሊከስ ፡ ሲችል ፡ ይህን ፡ ትቶ ፡ ባላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ክስ፡ ሊያቀርብ፡ አይችልም ። ለዚህ ፡ በጸሐፊዎችና ፡ በፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የሚሰጠው ፡ ምክንያት ፡ ያላ ግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስ ፡ የሚፈጠረው ፡ ደረጃው ፡ የበታች ፡ ከሆነ፡ የሕግ፡ ምንጭ ፡ ነው፡ የሚል ፡ ነው ። በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ የመጡት ፡ ጸሐፊዎች ፡ ግን ፡ ይህን ፡ የሕጎች ፡ ቅደም ፡ ተከተል ፡ አይቀበሉም ፡ ከሳሽም ፡ የፈለገውን ፡ የክስ ፡ ዓይነት ፡ ማቅረብ ፡ ይችላል ፡ ይላሉ ።

ሐ/ ፡ ከሳሽ ፡ በጥፋቱ ፡ ያልፈጠረው ፡ እንቅፋት ፡ ባጋጠመው ፡ ጊዜ ፡ ባላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ። ይህ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ የሚፈጠረው ፡ ከሳሽ ፡ የተዋዋለው ፡ ሰው ፡ ሲከስርና ፡ በውል ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ የማይቻል ፡ ሲሆን ፡ ነው ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ከሳሽ ፡ ግዴታውን ፡ በውሉ መሠረት ፡ በመፈጸሙ ፡ አንድ ፡ ሶስተኛ ፡ ወገን ፡ አለበቂ ፡ ምክንያት ፡ የበለጸገ ፡ ሲሆን ፡ ይህንን ፡ ሰው ፡ ሊከስ ፡ ይችላል ። እዚህ ፡ ላይ ፡ ክሱ ፡ በሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ረገድ ፡ የተከታይነት ፡ ደረጃ ፡ ያለው ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ፡ ምክንያቱም ፡ ከሳሽ ፡ ሊጠቀ ምበት ፡ የሚችለው ፡ ደንበኛውን ፡ ክሱን ፡ ማቅረብ ፡ ሳይችል ፡ ሲቀር ፡ ብቻ ፡ ነው ።

መ) ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስ ፡ መቅረብ ፡ የሚችልበት ፡ ሌላው ፡ ሁኔታ ፡ በውል ፡ ወይም ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ በተመሠረተ ፡ ክስ ፡ መጠቀም ፡ ሳይቻል ፡ ሲቀር ፡ ነው ። ጸሐፊዎችም ፡ ፍርድ ፡ ቤቶችም ፡ ይህን ፡ የሚያከራክር ፡ ሆኖ ፡ አላገኙትም ፡ ምክንያቱም ፡ ክሱ ፡ የተፈጠረበት ፡ ዋና ፡ ምክንያት ፡ እንደዚህ ፡ ባለው ፡ ሁኔታ ፡ ሀብቱ ፡ ለተቀነሰበት ፡ ወገን ፡ መድኅን ፡ ለመስጠት ፡ ስለሆነ ፡ ነው ። እንዲህ ፡ ሲሆን ፡ ሕጉ ፡ ላይ ፡ ሽፍጥ ፡ መፍጠር ፡ ወይም ፡ የሕጉን ፡ ቅደም ፡ ተከተል ፡ (ደረጃ) ፡ ማቃወስ ሊኖር ፡ አይችልም ።

## ክፍል ፡ ፪ ፡

## የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ።

### የሕጉ ፡ ምንጮች ።

በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ያለውን ፡ ሁኔታ ፡ ለመረዳት ፡ ጥናታችንን ፡ የምንጀምረው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍ ፡ ፪ሺ፩፻፷፪ ነው ። የምንጠቀመውም ፡ በፕሮፌሰር ፡ ቹቹ ኖቪች ፡ የተዘጋጀውን ፡ መጀመሪያ ፡ በፈረንሣይኛ ፡ በተጻፈው ፡ የአንቀጽ ፡ ፪ሺ፩፻፷፪ ፡ የእንግሊዘኛ ፡ ትርጉም ፡ ነው።[81] ይህን ፡ የምናደርግበት ፡ ምክንያት ፡ ፕሮፌሰሩ ፡ የተረጐሙት ፡ ከመጀመሪያው ፡ የፈረንሣይ ፡ ንድፍ ፡ ጋር ፡ የተቀራረበ ፡ በመሆኑና ፡ የፈረንሣይኛው ፡ ቍ. ፪ሺ፩፻፷፪ ፡ አጻጻፍ ፡ ከእንግሊዘኛው ፡ ትርጓሜ ፡ ይበልጥ ፡ ከአማርኛው ፡ ጋር ፡ የተቀራረበ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ።[82] የቍ. ፪ሺ፩፻፷፪ ፡ ምንጭ ፡ የፈረንሣይ ፡ ሕግ ፡ ሳይሆን ፡ የሞሮኮው ፡ የግዴታዎች ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፳፯ ፡ ነው ።[83]

ሕጉ ፡ በቀጥታ ፡ ከሞሮኮ ፡ የመነጨ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ፈረንሣይ ፡ በሞሮኮ ፡ በቅኝ ፡ ገዥነት ፡ ቆይታ ፡ ስለነበረና ፡ የሞሮኮው ፡ ሕግ ፡ የፈረንሣይን ፡ አስተሳሰብ ፡ የተከተለ ፡ ሆኖ ፡ ሁለቱም ፡ በጣም ፡ የተቀራረቡ ፡ ስለሆኑ ፡ ዞሮ ፡ ዞሮ ፡ ቍ ፡ ፪ሺ፩፻፷፪ ፡ ከፈረንሣይ ፡ ሕግ ፡ የመነጨ ፡ ነው ፡ ቢባል ፡ የተሳሳተ ፡ አይሆንም ።

የኛ ፡ ሕግ ፡ ከፈረንሣይ ፡ ሕግ ፡ በሁለት ፡ ነገር ፡ ይለያል ። ፩) በፈረንሣይ ፡ ሕግ ፡ ሕጉ ፡ የሚመነጨው ፡ ዳኞች ፡ ባሰቡት ፡ ፍትሐዊ ፡ አስተያየት ፡ ሲሆን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ግን ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ ሁኔታ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ውስጥ ፡ ተደንግጎ ፡ ይገኛል ። ፪) በቍ ፪ሺ፩፻፷፪ ፡ ውስጥ ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስ ፡ በሁለተኛ፡ ደረጃ ፡ መቅረብ ፡ አለበት ፡ የሚል ፡ አነጋገር ፡ አይገኝበትም ።

የቍ ፡ ፪ሺ፩፻፷፪ ፡ ዋናዎቹ ፡ ክፍሎች ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ።

ሀ) የከሳሽ ፡ ሀብት ፡ መቀነስ ፡

ለ) የተከሳሽ ፡ መበልጸግ ፡

ሐ) በሁለቱ ፡ መካከል ፡ ምክንያታዊ ፡ ግንኙነት ፡

መ) ለብልጽግናው ፡ ምክንያት ፡ እጦት ፡

### ፩/ የክሱ ፡ ተከታይነት ፡

በዚህ ፡ ክፍል ፡ ይህ ፡ የተከታይነት ፡ ጠባይ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ይገኝ፡ እንደሆነና ፡ መገኘትስ ፡ እንዳለበት ፡ እንወያያለን ። ለዚህ ፡ ውጤት ፡ የሚያመቸው ፡ ዘዴ ፡ በፈረንሣይ ፡ ሕግ ፡ የተመለከትናቸውን ፡ ሁለት ፡ ንጥረ ፡ አሳቦችን ፡ መነሻ ፡ በማድረግ ፡

ሀ) በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የሕጎች ፡ ቅደም ፡ ተከተል ፡ ይሰራ ፡ እንደሆንና ፡
ለ) በሕጉ ፡ ላይ ፡ ሽፍጥ ፡ እንዳይፈጸም ፡ የሚለው ፡ መሠረተ ፡ አሳብ ፡ ክሱን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የተከታይነት ፡ ደረጃ ፡ ይሰጠው ፡ እንደሆነ ፡ መመልከት ፡ ነው ።

---

81. በግዴታዎች ፡ ትምህርት ፡ ሁለተኛ ፡ ክፍል ፡ ለተማሪዎች ፡ እንደተሰጠ ፡
82. የቍ. ፪ሺ፩፻፷፪ ፡ የእንግሊዘኛ ፡ ትርጉም ፡ የተለየ ፡ ነው ።
83. በኮዲፊኬሽን ፡ ኮሚሽን ፡ የተዘጋጁ ፡ ገላጭ ፡ ማስታወሻዎች ገጽ ፡ ፶፮
84. በቻሊስ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ ገጽ ፡ ፩፻፸ ፡ ውስጥ ፡ እንደሚገኘው ።

ሀ) የሕግ ፡ ምንጮች ፡ ቅደም ፡ ተከተል ።

በኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ አላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ አንድ ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ አጠቃላይ ፡ ሃሳብ ፡ እንዳለና ፡ ይህም ፡ ከፈረንሣይ ፡ ሕግ ፡ የተለየ ፡ መሆኑን ፡ አይተናል ፡ ማለትም ፡ እንደ ፡ ፈረንሣዩ ፡ ሕግ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ያላ ግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ሕግ ፡ ከፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ውሳኔዎች ፡ የመነጨ ፡ አይደለም ።[85] በሕ ግ ፡ አውጪው ፡ ክፍል ፡ የተፈጠረ ፡ ስለሆነም ፡ አላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ላይ ፡ የሚመ ሠረት ፡ ክስ ፡ ምንጩ ፡ ከሌሎች ፡ በሕግ ፡ ከተደነገጉ ፡ የግዴታ ፡ ምንጮች ፡ ጋር ፡ በእ ኩልነት ፡ ደረጃ ፡ ይገኛል ። ስለዚህ ፡ አንድ ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግን ፡ የሚያስከትል ፡ ሁኔታ ፡ ሲፈጠር ፡ ሕጉ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ክስ ፡ እንዲቀርብ ፡ ይፈቅዳል ። ያላግባብ ፡ መበልጸግን ፡ የሚመለከት ፡ ሁኔታ ፡ በተፈጠረ ፡ ቍጥር ፡ ሌላ ፡ የሚያዋጣ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ይቻላል ፡ ወይስ ፡ አይቻልም ፡ ሳይባል ፡ ይኸንኑ ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ ይቻላል ። በዚህ ፡ ዓይነት ፡ በፈረንሣይ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ለክሱ ፡ ተከታይነት ፡ ምክን ያት ፡ የሆነው ፡ የሕጎች ፡ ቅደም ፡ ተከተል ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ውስጥም ፡ ምክንያት፡ ሆኖ ፡ ሊያገለግል ፡ አይችልም ።

ለ) በሕጉ ፡ ላይ ፡ ሽፍጥ ፡ መፈጸም ፡ ወይም ፡ "ፍሮድ ፡ አ ፡ ላ ፡ ሉዋ" ።

ይህስ ፡ ምክንያት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ አለ ? ባይኖርስ ፡ ሊኖር ፡ ይገባዋልን ? በመጀመሪያ ፡ ይህ ፡ ሃሳብ ፡ በማናቸውም ፡ ሕግ ፡ ቢሆን ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ እንዳማይቀ ርብ ፡ ማስታወስ ፡ ያስፈልጋል ። ሃሳቡ ፡ ግን ፡ ከሕግ ፡ መንፈስ ፡ ጋር ፡ የተዋሃደ ፡ ነው ። ጸሐፊዎችና ፡ ዳኞች ፡ አንዱ ፡ ሕግ ፡ በተዘዋዋሪ ፡ ዘዴ ፡ እንዲፈርስ ፡ መፍ ቀድ ፡ ጠቅላላውን ፡ የሕግ ፡ አቋም ፡ ማናጋት ፡ እንደሆነ ፡ መግለጻቸውን ፡ አይተናል ። በኢትዮጵያው ፡ ሕግ ፡ ውስጥም ፡ አንድ ፡ ክስ ፡ በሕግ ፡ ታግዶ ፡ መቅረብ ፡ ሳይችል ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስን ፡ ማቅረብ ፡ ሕጉን ፡ የሚያፈርስ ፡ ዘዴ ፡ መሆኑን ፡ መረ ዳት ፡ ይቻላል ። ለምሳሌ ፡ በይርጋ ፡ የታገደውን ፡ በውል ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ክስ ፡ ከሳሹ ፡ ማቅረብ ፡ ሲያቅተው ፡ ባላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ክስ ፡ ቢያቀርብ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፩ሺ፰፻፵፭ ፡ ፈጽሞ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ይሆን ፡ ነበር ። ተመሳሳይ ፡ የሆኑትም ፡ የማገድ ፡ ጠባይ ፡ ያላቸው ፡ ሕጎች ፡ ሁሉ ፡ ይኸው ፡ ዕድል ፡ ይደርሳቸው ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ሕጉ ፡ ሲወጣ ፡ የተጣመረና ፡ አንዱን፡ አንዱ ፡ እያፈረሰ ፡ ትርጉም ፡ የማያሳጣው ፡ መሆን ፡ አለበት ፡ ከተባለ ፡ ይህን ፡ አፍ ራሽ ፡ የሆነውን ፡ አጠቃቀም ፡ መቀበል ፡ ከታቀደው ፡ ሃሳብ ፡ መራቅ ፡ ይሆናል ።

እዚህ ፡ መደምደሚያ ፡ ላይ ፡ በሌላ ፡ አቅጣጫ ፡ መድረስ ፡ እንችላለን ። በፈረን ሣይ ፡ ሕግ ፡ በተከታይነትና ፡ በ"በቂ ፡ ምክንያት" መካከል ፡ መወራረስ ፡ እንዳለ ፡ አይተናል ። አስተሳሰቡ ፡ ሕጉ ፡ አንድ ፡ ክስ ፡ በሚያግድበት ፡ ጊዜ ፡ ለሚገኘው ፡ ብል ጽግና ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ስለሚሆን ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስን ፡ ማቅረብ ፡ አይቻ ልም ፡ የሚል ፡ ነበር ። ይህ ፡ አስተሳሰብ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ይሰራ ፡ እንደሆን ፡ እን መለከታለን ። በቍ. ፪ሺ፩፻፷፪ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ካለ ፡ ክሱን ፡ ማቅረብ ፡ አይቻልም ። በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ለመበልጸግ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ የሚሆኑት ፡ ውሎች ፡ ወይም ፡ ሕጉ ፡ እራሱ ፡ ናቸው ።

እንግዲህ ፡ ያሁኑ ፡ ጥያቄያችን ፡ አንድ ፡ ክስ ፡ እንዳይቀርብ ፡ የሚያግድ ፡ ሕግ ፡ አንድ ፡ ውል ፡ ወይም ፡ የሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ለብልጽግና ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ እንደሚሆን፡ ሁሉ ፡ ይህም ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ሊሆን ፡ ይችላልን ? የሚል ፡ ነው ። ይህን ፡ ከመመለ

---

5. ኒኮላስ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ገጽ ፡ ፻፲፴፬

ሳችን ፡ በፊት ፡ አንድ ፡ ምሳሌ ፡ እንውሰድ ። አንድ ፡ አቅመ ፡ አዳም ፡ ያላደረሰ፡ ልጅ በወራሽነት ፡ ይጠራል ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በቍ ፡ ፰፻፸፪ ፡ (፩) ፡ መሠረት ፡ ሞግዚቱ ፡ የውርሱን ፡ ዋጋ ፡ ዝርዝር ፡ ያዘጋጃል ። ከዚህም ፡ ንብረት ፡ ውስጥ ፡ ሞግዚቱ ፡ የሚወርሰው ፡ ንብረት ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በዝርዝሩ ፡ ውስጥ ፡ ሳይጠቀሰው ፡ ይቀራል ። ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ስራውን ፡ ይተዋል ። የሚገባውን ፡ ድርሻ ፡ እንዲቀበል ፡ በቍ ፡ ፩ሺ፪፻፯ ፡ መሠረት ፡ ክስ ፡ ያቀርባል ።

ነገር ፡ ግን ፡ ቍ ፡ ፰፻፹፪ ፡ (፪) ፡ የሚያዘውን ፡ ባለመፈጸሙ ፡ ክሱ ፡ ውድቅ ፡ ይሆናል ። ልጁ ፡ እንግዲህ ፡ በዚሁ ፡ መጠን ፡ በይበልጥ ፡ በለጸገ ፡ ማለት ፡ ነው ። እዚህ ፡ ላይ ፡ የሞግዚቱንም ፡ ድርሻ ፡ በመውሰድ ፡ ያገኘው ፡ መበልጸግ ፡ በውል ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ስላልሆነ ፡ የመበልጸጉ ፡ ምክንያት ፡ ሕጉ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው ።

ይህ ፡ ምሳሌ ፡ ሕጉ ፡ በሁለት ፡ መንገድ ፡ የመበልጸግ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ሊሆን፡ እንደሚችል ፡ ያስረዳል ። የልጁ ፡ በውርስ ፡ መበልጸግ ፡ በቀጥታ ፡ በሕጉ ፡ ምክንያት ፡ መበልጸጉን ፡ ያሳያል ፡ በሞግዚቱ ፡ ቸልተኛነት ፡ ምክንያት ፡ የበለጸገው ፡ ግን ፡ በተዘዋዋሪ ፡ መንገድ ፡ ነው ። መንገዱ ፡ የተለያየ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ በሁለቱም ፡ ሁኔታ ፡ ለብልጽግናው ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ ሕጉ ፡ ነው ። እንደዚሁም ፡ በማንኛቸውም ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ሕግ ፡ ሌላ ፡ ክስ ፡ በሚያግድበት ፡ ጊዜ ፡ ለብልጽግናው ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ ሕጉ ፡ ነው ፡ ሊባል ፡ ይቻላል ። እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ሁኔታ ፡ ሲያጋጥም ፡ ሕጉ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ስለሚፈጥር ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስ ፡ ሊቀርብ ፡ አይችልም ። ስለዚህ ፡ "የተከታይነት ፡ ጠባይ" ፡ ከ"በቂ፡ ምክንያት፡" ጋር፡ ተሳስሮ ፡ ሲቀርብ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ እንዳለ ፡ ተረጋገጠ ፡ ማለት ፡ ነው ።

*መደምደሚያ ።*

በኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ የቀረበ ፡ ስለ ፡ ተከታይነት ፡ ወይም ፡ የሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ተጠቃሽነት ፡ ጉዳይ ፡ የሚናገር ፡ ቍጥር ፡ የለም። ስለዚህ ፡ በሌላ ፡ አኳኋን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ይገኝ ፡ እንደሆን ፡ ለመረዳት ፡ የፈረንሳይን ፡ ሁለት ፡ አጠቃላይ ፡ ሃሳቦች ፡ መረመርን ።

ሀ) የተከታይነት ፡ ጠባይ ፡ በሕጎች ፡ ቅደም ፡ ተከተል ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ሲሆን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ቦታ ፡ እንደሌለው ፡ አይተናል ። በኢትዮጵያ ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስ ፡ እንደሌሎቹ ፡ ክሶች ፡ ሁሉ ፡ በሕግ ፡ አውጪው ፡ ክፍል ፡ የተፈጠረ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ምንጫቸው ፡ አንድ ፡ የሆነ ፡ ክሶች ፡ በደረጃ ፡ ሊለያዩ ፡ አይችሉም ።

ለ) ፡ በሕጉ ፡ ላይ፡ ሽፍጥ ፡ እንዳይፈጸም ፡ ሲባል፡ የሚፈጠረው፡ የ"ተከታይነት"፡ ደረጃ ፡ ግን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ትርጉምና ፡ ኀላፄ ፡ አለው ። በተጨማሪ ፡ ቍ ፡ ፪ሺ፩፻፴፪ ፡ የሚያዘው ፡ ያለ ፡ "በቂ ፡ ምክንያት ፡" የተባለው ፡ ሁኔታ ፡ ክሱን ፡ ወደ ፡ ሁለተኛ ፡ ደረጃነት ፡ ያወርደዋል። ስለዚህ ፡ የተከሳሹ፡ መበልጸግ፡ በ"በቂ፡ ምክንያት" የተደገፈ ፡ ሲሆን ፡ ክሱ ፡ ሊቀርብ ፡ አይችልም ።[86]

---

86. በሞሮኮም ፡ "ለተከታይነት" የተሰጠው ፡ ትርጓሜ ፡ እዚህ ፡ ከተሰጠው ፡ ትርጓሜ ፡ ጋር ፡ የሚስማማ ፡ ነው ። ይህ ፡ የሆነበት ፡ ምክንያት ፡ በሁለቱም ፡ ውስጥ ፡ መነሻ ፡ የሆኑት ፡ ሃሳቦች ፡ ተመሳሳይ ፡ ስለሆኑ፡ ነው ።
የሕጐች ፡ ቅደም ፡ ተከተልን ፡ በመከተል ፡ የተፈጠረው ፡ አስተሳሰብ ፡ ሕግ ፡ አውጪው ፡ ክፍል ፡ ለሁሉም ፡ ክሶች ፡ አንድ ፡ ምንጭ ፡ በመፍጠሩ ፡ በሞሮኮ ፡ ውስጥ ፡ ቦታ ፡ የለውም ።
(ድራኪዲስ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ቍ ፴፯ ፡ ገጽ ፺፻፱) እንዲሁም ፡ በሞሮኮ ፡ ሕግ ፡ መሠረት፡ በሕግ ፡ ምክንያት ፡ ሌላው ፡ ክስ ፡ ሲታገድ ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ አይቻልም ። ድራኪዲስ ፡ አንድ ፡ የፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ ይጠቅሳል ፡ (ራባት-፮ ማርስ ፡ ፲፱፻፶፭ ፡ ጋዜት ፡ ትሪቡናል ፡ ደማሮክ ፲ ፡ ኖቬምበር ፡ ፲፱፻፶፭ ፡ ገጽ ፡ ፩፻፴፫) ይህ ፡ ጉዳይ ፡ አንድ ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ በተፈጠረ ፡ ግዴታ ፡ ላይ፡ የተመሠረተ ፡ ክስ ፡ በይርጋ ፡ ምክንያት ፡ ከታገደ ፡ ወዲያ ፡ ስለቀረበ ፡ ውድቅ ፡ እንደሆነ ፡ የሚያመለክት ፡ ነው ።